የፌደራል የታክስ አስተዳደር

ነሐሴ-2018ዓ.ም

ክፍል አንድ፡- 1. ጠቅላላ ድንጋጌ

- የታክስ አስተዳደሩ ይበልጥ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተገማችነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ የአገር ውስጥ ታክሶች ሁሉ የሚመሩበት ራሱን የቻለ የታክስ አስተዳደር አዋጅ እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ፤
- በታክስ ህጎች አተረጓገም ረገድ በታክስ አስተዳደሩ ውስጥ በሚፈጠረው ልዩነት ምክንያት ታክስ ከፋዩ ሲያጋጥመው የነበረውን እንግልት ለማስቀረት የሚያስችል ወጥነት ያለው የአተረጓጎም ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ የሚያስፈልግ በመሆኑ፤
- ታክስ ከፋዮች በታክስ ውሳኔ ረገድ የሚኖራቸውን ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉበት ተደራሽነት ያለው፣ በሚገባ የተደራጀ እና የተቀላጠፈ ውሳኔ በመስጠት የሚያስችል የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

2. ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ማለት

- በአንድ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ የአንድ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ ዋጋ ነው የሚባለው የዕቃው፣ የንብረቱ፣ የአገልግሎቱ ወይም የጥቅሙ የወቅቱና የቦታው መደበኛ የገበያ ዋጋ ነው።
- በአንድ የተወሰነ ጊዜ እና ቦታ የአንድን ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ፡-
  - ዋጋውን ለመወሰን ባልተቻለው ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም እና ማንኛውም ሌላ ተመሳሳይ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም በሚያስገኘው ትክክለኛ ዋጋ መካከል ላለው ልዩነት ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ የሚገኘው ዋጋ ዋጋውን ለመወሰን ያልተቻለው ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ሆኖ ይወሰዳል።
  - ለዚህ አፈጻፀም አንድ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ከሌላ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ጋር ተመሳሳይ ነው የሚባለው ከሌላው ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ጋር በባህሪይ፣ በጥራት፣ በብዛት በሚሰጠው አገልግሎት በሚይዛቸው ቁሶችና በመልካም ስም ተመሳሳይ ወይም በሚቀራረብ ሁኔታ ተመሳሳይ የሆነ እንደሆነ ነው።

3. ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ማለት

- ሁለት ሰዎች ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ናቸው የሚባለው ከሁለቱ አንዱ ሰው በሌላኛው ሰው ትዕዛዝ፣ ጥያቄ፣ አስተያየት ወይም ፍላጎት መሠረት ይንቀሳቀሳል ተብሎ ሲገመት ወይም ሁለቱም ሰዎች በሌላ ሦስተኛ ወገን ትዕዛዝ፣ ጥያቄ፣ ሃሣብ ወይም ፍላጎት መሠረት ይንቀሳቀሳሉ ተብሎ ሲታመን ነው።
- በተጨማሪም የሚከተሉት ሰዎች ግንኙነት ያላቸው ሰዎች እንደሆኑ ይቆጠራል፡-
  - ➢ ባለሥልጣኑ ከሁለቱ አንዱ በሌላኛው ትዕዛዝ፣ ጥያቄ፣ አስተያየት ወይም ፍላጎት መሠረት አይንቀሳቀስም ብሎ ካላመነ በስተቀር፣ አንድ ግለሰብና የዚህ ግለሰብ ዘመድ፤
  - ➢ አንድ ድርጅት ወይም የዚህ ድርጅት አባል በራሱ ወይም ግንኙነት ካላቸው ሰዎች ጋር በመሆን በቀጥታ ወይም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑና በተሳሰሩ ድርጅቶች አማካይነት የድርጅቱን ሃያ አምስት በመቶ (25%) ወይም ከዚያ በላይ የመምረጥ፣ የትርፍ ድርሻ ወይም የካፒታል ደርሻ መብት የሚቆጣጠር ሲሆን ድርጅቱና የድርጅቱ አባል ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ናቸው።
  - ➢ ሁለት ድርጅቶች ግንኙነት ያላቸው ናቸው የሚባሉት አንድ ሰው ብቻውን ወይም ግንኙነት ካለው ሰው ጋር በመሆን የሁለቱን ድርጅቶች የትርፍ ድርሻ ወይም ካፒታል በቀጥታ ወይም በሌሎች በተሳሰሩ ድርጅቶች አማካይነት ሃያ አምስት በመቶ (25 %) ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የመምረጥ መብት፣ የተቆጣጠረ እንደሆነ ነው።

3. ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ማለት

- የአንድ ግለሰብ ዘመዶች ናቸው የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፤
  - ➢ የትዳር ጓደኛ፤ የአንድ ግለሰብ የትዳር ጓደኛ የሚባሉት፡
    - ✓ ግለሰቡ/ሰቧ በህጋዊ መንገድ ያገባው/ችው፣
    - ✓ ጋብቻ ሳይኖር ከግለሰቡ/ቧ ጋር እንደባልና ሚስት አብሮ/ራ የሚኖር/የምትኖር፤
  - ➢ ቅድመ አያት፣ አያት፣ ወደታች የሚቆጠር ዘመድ፣ ወንድም፣ እህት፣ አጎት፣ አክስት፣ የወንድም ልጅ፣ የእህት ልጅ፣ የእንጀራ እናት፣ የእንጀራ አባት፣ የጉዲፈቻ ልጅ፤ እና የእነዚህ ግለሰቦች ባል ወይም ሚስት፤
  - ➢ የጉዲፈቻ ልጅ ወላጅ፣ ወይም የእርሱ/ሷ ባል ወይም ሚስት፤ አንድ የጉዲፈቻ ልጅ ከጉዲፈቻ አድራጊዎች የአንደኛ ደረጃ ዘመዶች ጋር ዝምድና እንዳለው ይቆጠራል።

የታክስ ህጎችን ስለማስተዳደር

1. የባለሥልጣኑ ኃለፊነት

- የታክስ ሕጎችን ሥራ ላይ የማዋልና የማስፈፀም ኃላፊነት ለባለሥልጣኑ የተሠጠ ነው።
- በዚህ አዋጅ ትርጉም **“ባለሥልጣን”** ማለት፣

  ሀ) የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር፣

  ለ) የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ፣

  ሐ) የድሬዳዋ ገቢዎች ቢሮ ማለት ነው፤

2. የመተባበር ግዴታ

- ማናቸውም የፌዴራል እና የክልል መንግሥት፣
- የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣
- ኤጀንሲ ወይም ሌላ አካል፣
- የአካባቢ አስተዳደሮች፣
- ማህበራት፣
- ድርጅቶች፣
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የታክስ ሕጎችን በማስፈፀም ረገድ ከባለሥልጣኑ ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

3. ታክስ ከፋዮች

3.1. ታክስ ከፋዮችን ስለመመዝገብ

- አስቀድሞ የተመዘገበ ካልሆነ በስተቀር በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሰው በባለሥልጣኑ ዘንድ ለመመዝገብ ማመልከት አለበት፡፡
- ነገር ግን ይህ ድንጋጌ፡
  - በኢትዮጵያ የሚያገኘው ገቢ ብቻ በገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌ መሰረት በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው የትርፍ ድርሻ፣ ሮያሊቲ፣ ወለድ፣ የስራ አመራር ክፍያ፣ የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ ወይም የመድን አረቦን ከኢትዮጵያ ውስጥ ያገኘን ሰው እና በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ የመዝናኛ አገልግሎት ሰጪዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም እንዲሁም
  - በሠንጠረዥ "መ" መሰረት የሚጣለው የመጨረሻ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ብቻ ያለው ግለሰብ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

3. ታክስ ከፋዮች ...

3.1. ታክስ ከፋዮችን ስለመመዝገብ ...

ለምዝገባው የሚቀርበው ማመልከቻ፡-

- ባለሥልጣኑ ባጸደቀው ቅጽ መሠረት መቅረብ ይኖርበታል፡፡
- **"የጸደቀ ቅጽ"** ማለት በዚህ አዋጅ ድንጋጌ መሰረት ሲሆን
- በታክስ ከፋይ የሚቀርብ ማንኛውም የታክስ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ፣ ማስታወቂያ፣ መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ በፀደቀው ቅጽ መሠረት እንደቀረበ የሚቆጠረው ሰነዱ፡-
    - ለሰነዱ ዓይነት **በባለሥልጣኑ በፀደቀ**_ቅጽ መሠረት የቀረበ፣
    - ማንኛውንም **ተያያዥ ሰነዶች ጨምሮ ቅጹ የሚጠይቀውን መረጃ የያዘ**፣ እና
    - ቅጹ በሚጠይቀው መሠረት **የተፈረመ** ሲሆን ነው፡፡

3. ታክስ ከፋዮች ....

3.1. ታክስ ከፋዮችን ስለመመዝገብ ...

- ታክስ ከፋዩ ለታክስ የመመዝገብ ግዴታ ካለበት ቀን አንስቶ **በ21 ቀናት** ውስጥ ወይም ባለሥልጣኑ በፈቀደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት።
- ባለሥልጣኑ ለመመዝገብ ያመለከተው ሰው በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ሲያምንበት ይመዘግበዋል፤ **የምስክር ወረቀት** አዘጋጅቶ ይሰጠዋል።
- ባለሥልጣኑ ለመመዝገብ ማመልከቻ ያቀረበውን ሰው ጥያቄያ ልተቀበለው ከሆነ የምዝገባውን ጥያቄ የማይቀበለው መሆኑን ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት **14 ቀናት** ውስጥ ለምዝገባ ላመለከተው ሰው በጽሁፍ ያሳውቀዋል።
- የአንድ ሰው ምዝገባ ተፈፃሚ የሚሆነው የዚህን ሰው ምዝገባ በሚያረጋግጠው የምስክር ወረቀት ላይ ከተመለከተው ቀን ጀምሮ ነው።
- የታክስ ከፋዮች ምዝገባ የሚከናወነው ኢትዮጵያ የተቀበለችውን የዓለም አቀፍ የኢንዱስትሪ ምደባ ደረጃ መሰረት በማድረግ ነው።

3. ታክስ ከፋዮች ....

3.2. ለውጦችን ስለማሳወቅ

- ማንኛውም የተመዘገበ ሰው
  - ስሙ፣ ቋሚ አድራሻው ወይም የፖስታ አድራሻው፣ የተቋቋመበት መተዳደሪያ ደንብ ወይም ዋንኛ የሥራ እንቅስቃሴው ወይም እንቅስቃሴዎቹ ከተለወጡ፤
  - ከባለሥልጣኑ ጋር ግንኙነት የሚያደርግበት የባንክ አድራሻ፣ የኤሌክትሮኒክ አድራሻ ከተለወጠ፤
  - ባለሥልጣኑ በመመሪያ የሚወሰናቸው ሌሎች ዝርዝሮች፣ በተመለከተ ለውጥ ሲከሰት ለውጡ በተከሰተ **በ21 ቀናት** ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤
- የተመዘገበ ሰው የለውጥ ማስታወቂያ ሲያቀርብ ይህ ሰው በሌላ የታክስ ሕግ ለአንድ ለተለየ ታክስ ካደረገው ምዝገባ ጋር በተያያዘ ተመሳሳይ ለውጦችን ማስታወቅን በተመለከተ የተጣለበትን የማስታወቅ ግዴታ እንደተወጣ ይቆጠራል።

3. ታክስ ከፋዮች ....

3.3. ምዝገባን ስለመሰረዝ

- የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ለሁሉም የታክስ ሕጐች የተጣለበት የመመዝገብ ግዴታ ሲቋረጥ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ለባለስልጣኑ ማመልከት አለበት፣
- ምዝገባን ለማሰረዝ የሚቀርበው ማመልከቻ በሁሉም የታክስ ሕጐች የተጣለበት **የመመዝገብ ግዴታ ከተቋረጠበት ቀን አንስቶ ባሉት 30 ቀናት** ውስጥ ወይም ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት።
- አንድ ሰው በዚህ መሰረት ለመሰረዝ ማመልከቻ ካቀረበ በሌላ የታክስ ሕግ ለአንድ የተለየ ታክስ የተደረገው ምዝገባ እንዲሰረዝለት ጭምር እንዳመለከተ ተደርጎ ይወሰዳል።
- አንድ ሰው በዚህ መሠረት ማመልከቻ ሲያቀርብ ባለሥልጣኑ ይህ ሰው ሥራውን ያቆመ መሆኑንና በሁሉም የታክስ ሕጎች የመመዝገብ ግዴታ የሌለበት መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ለዚህ ሰው የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ምዝገባውን ይሰርዝዋል።

3. ታክስ ከፋዮች ....

3.3. ምዝገባን ስለመሰረዝ ...

- ምዝገባ የተሠረዘ መሆኑን የሚገልፀው ማስታወቂያ ማመልከቻው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ለአመልካቹ መሰጠት የሚኖርበት ሲሆን፣ ባለሥልጣኑም ማመልከቻው ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት 90 ቀናት ውስጥ የታክስ ከፋዩን የታክስ ጉዳዮች በተመለከተ የመጨረሻ ኦዲት ሊያደርግ ይችላል፡፡
- አንድ ሰው ምዝገባ እንዲሰረዝለት ጥያቄ ያላቀረበ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ይህ ሰው ሥራውን ሙሉ በሙሉ ማቆሙን እና ለታክስ ሕጐች ዓላማ የመመዝገብ ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንዲሁም የተፈጥሮ ሰው ከሆነ መሞቱን፣ ኩባንያ ከሆነም መፍረሱን፣ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ሕልውናው የተቋረጠ መሆኑን ሲያምንበት ለታክስ ከፋዩ ወይም ለታክስ እንደራሴው የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ምዝገባውን ይሰርዛል፡፡
- በራሱ አመልክቶ የሚሰረዘውም ሆነ ባለሥልጣኑ ሳያምንበት የሚደረግ የአንድ ሰው ምዝገባ መሰረዝ በሌላ ታክስ ሕግ ለአንድ የተለየ ታክስ ዓላማ ሲባል የተደረገ ምዝገባ መሰረዝንም ይጨምራል፡፡
- ሆኖም የአንድ ሰው የምዝገባ መሰረዝ በሌላ ታክስ ሕግ አንድን የተለየ ታክስ የሚመለከት ሲሆን፣ በዚያ የታክስ ሕግ ምዝገባ መሰረዝን በሚመለከት የሠፈሩትን ግዴታዎች ማሟላት ግዴታ ይሆናል፡፡

4. ስለታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር

4.1. ታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር

- ታክስ ከፋዮችን ለመለየት እንዲቻል ባለሥልጣኑ ለታክስ ሕጐች ዓላማ ሲባል ለተመዘገበ ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር በሚል የሚታወቅ ቁጥር ይሰጣል፤
- ታክስ ከፋዩም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን የታክስ ሕጎች በሚያዙት መሠረት መጠቀም አለበት፡፡

4. ስለታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር...

4.2. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ስለመሰጠት

- ለሁሉም የታክስ ሕጎች አንድ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሚሰጥ ሲሆን አንድ ታክስ ከፋይ በማንኛውም ጊዜ አንድ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ብቻ ይኖረዋል፡፡
- ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ የታክስ መለያ ቁጥር የሚሰጠው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ማስታወቂያ በመስጠት ይሆናል፡፡

4. ስለታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ....

4.3. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አጠቃቀም

- የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጠው ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን በማንኛውም የታክስ ማስታወቂያ፣ ማስታወቂያ ወይም ለታክስ ሕግ ዓላማ ሲባል በሚቀርብ ወይም ጥቅም ላይ በሚውል ሰነድ ወይም በታክስ ሕግ መሠረት በሚዘጋጅ ሰነድ ላይ መግለጽ ይኖርበታል፤
- ታክስ ከፋዩ ታክስ ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ላለበት ሰው ክፍያዎች በሚፈጽምበት ጊዜ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ማሣወቅ አለበት።
- የንግድ ሥራ ለመሥራት ፈቃድ ይሰጠው ዘንድ ማመልከቻ የሚያቀርብ ታክስ ከፋይ ፈቃድ ለሚሰጠው ባለሥልጣን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን መስጠት አለበት።
- የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሚሰጥ የመንግሥት አካል ወይም ተቋም ታክስ ከፋዩ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ሳያቀርብ ፈቃድ መስጠት አይችልም።

4. ስለታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ....

4.3. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አጠቃቀም...

- ታክስ ከፋዩ ፈቃዱን በሚያድስበት ጊዜ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ማቅረብ የሚጠበቅበት የመጀመሪያው የፈቃድ ማመልከቻ ከቀረበ ወዲህ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ የተቀየረ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
- የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ለተሰጠው ሰው ብቻ የሚያገለግል ስለሆነ በሌላ ሰው ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፡፡
- ነገር ግን የታክስ ወኪል የአንድን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ ይኸውም፡-
  - የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ ባለቤት የሆነው ሰው የታክስ ወኪል የታክስ መለያ ቁጥሩን ለመጠቀም እንዲችል በጽሑፍ ሲፈቅድለት፣ እና
  - የታክስ ወኪሉ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ለታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ ባለቤት የታክስ ጉዳዮች ብቻ ሲጠቀምበት ነው፡፡

4. ስለታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ....

4.4. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥርን ስለመሰረዝ

- ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የአንድን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ለመሠረዝ ይችላል፡-
  - የታክስ ከፋዩ ምዝገባ ሲሰረዝ፤
  - የታክስ ከፋዩ እውነተኛ ማንነት ባልሆነ ማንነት የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ የተሰጠ እንደሆነ፤
  - ታክስ ከፋዩ ጥቅም ላይ ያለ ሌላ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ያለው እንደሆነ፤
- ባለሥልጣኑ በማንኛውም ጊዜ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የአንድን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር በመሰረዝ አዲስ የታክስ መለያ ቁጥር ሊሰጠው ይችላል፡፡

5. የታክስ እንደራሴ ግዴታዎች

- አንድ የታክስ እንደራሴ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብንና ታክስ መክፈልንም ጨምሮ የታክስ ሕግ በታክስ ከፋዩ ላይ የሚጥለውን ማንኛውም ግዴታ የመወጣት ኃላፊነት አለበት።
- **"የታክስ እንደራሴ"** ማለት ታክስ ከፋዩን በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውንም ገንዘብ ለመቀበል ወይም ለመክፈል ኃላፊነት ያለበት ግለሰብ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡-
  - የሽርክናን ማህበር በተመለከተ የሽርክና ማህበሩ ሽሪክ ወይም ሥራ አስኪያጅ፣
  - ኩባንያን በተመለከተ የኩባንያው ዳይሬክተር፤
  - ችሎታ የሌለውን ግለሰብ በተመለከተ ችሎታ የሌለውን ግለሰብ በመወከል ወይም ለዚህ ግለሰብ ጥቅም ገቢ የሚቀበል ህጋዊ ወኪል፣
  - የአንድ ታክስ ከፋይ ሀብት ተረካቢ በተመለከተ የታክስ ከፋዩ ባለአደራ፣
  - ማንኛውንም ታክስ ከፋይ በተመለከተ ለታክስ ሕጎች ዓላማ ሲባል ባለሥልጣኑ በጽሁፍ በተሰጠ ማስታወቂያ የታክስ ከፋዩ የታክስ እንደራሴ እንደሆነ ያስታወቀው ግለሰብ ነው።

5. የታክስ እንደራሴ ግዴታዎች....

- አንድ ታክስ ከፋይ ሁለትና ከሁለት በላይ የታክስ እንደራሴዎች ያሉት እንደሆነ እያንዳንዱ የታክስ እንደራሴ ለተመለከቱት ግዴታዎች የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት አለበት፤ ሆኖም ግን ከታክስ እንደራሴዎቹ መካከል አንዱ የታክስ ወኪል ግዴታዎችን መወጣት ይችላል፡፡
- በታክስ እንደራሴ መከፈል የሚኖርበት ታክስ በታክስ እንደራሴው ይዞታ ወይም ቁጥጥር ሥር ባለው ገንዘብ ወይም ሀብት መጠን ከታክስ እንደራሴው መሰብሰብ አለበት፡፡
- ነገር ግን በታክስ እንደራሴው መከፈል የነበረበት ታክስ ሳይከፈል ሲቀር የታክስ እንደራሴው በታክስ እንደራሴነቱ ታክሱን ለመክፈል የግል ኃላፊነት የሚኖርበት የታክስ እንደራሴው፡-
  - የተቀበለውን ወይም ሊቀበለው የሚችለውንና ታክስ የሚከፈልበትን ገንዘብ ያጠፋ፣ ለሌላ ዓላማ ያዋለ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ፣
  - የታክስ ከፋዩ ሀብት የሆኑ እና በታክስ እንደራሴው ይዞታ ሥር የነበሩ ወይም ታክስ መከፈል ከነበረበት ጊዜ በኋላ በይዞታው ሥር የሆኑ እና ለታክሱ ክፍያ ሊውሉ የሚችሉ ንብረቶችን ወይም ገንዘብ ያስተላለፈ ወይም በከፊል ለሌላ የሰጠ እንደሆነ ነው፡፡

5. የታክስ እንደራሴ ግዴታዎች....

- የታክስ እንደራሴው ለታክስ ክፍያ የግል ኃላፊነት የማይኖርበት፡
  - በታክስ እንደራሴው የተከፈለው ገንዘብ የዋለው ለታክስ ከፋዩ ጥቅም ሲሆንና የተከፈለው ገንዘብ በሕግ ከታክስ ከፋዩ ታክስ የመክፈል ግዴታ ቅድሚያ ሲኖረው፤ ወይም
  - ገንዘቡ በተከፈለበት ጊዜ የታክስ እንደራሴው ታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳ ያለበት መሆኑን ካላወቀ ወይም ሊያውቅ የማይችል ከሆነ ነው።
- የታክስ እንደራሴው በታክስ ከፋዩ ላይ በታክስ ሕግ የተጣለውን ማንኛውንም ግዴታ ሳይወጣ ቢቀር ታክስ ከፋዩ ካለበት ማንኛውም ግዴታ ነፃ ሊያደርገው አይችልም።

6. ስለሠነዶች

6.1. መዝገብ የመያዝ ግዴታዎች

- ለታክስ ሕግ ዓላማ ሲባል አንድ ታክስ ከፋይ በታክስ ሕግ መያዝ ያለባቸውን ሰነዶች በኤሌክትሮኒክ መልክ ጨምሮ የመያዝ ግዴታ ያለበት ሲሆን እነዚህም ሰነዶች የሚያዙት፡
  - በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ፣
  - በኢትዮጵያ ውስጥ፤ እና
  - የታክስ ከፋዩን የታክስ ግዴታ በግልጽ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ መሆን አለበት።
- በታክስ ሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር አንድ ታክስ ከፋይ ከላይ የተመለከቱትን ሰነዶች ከሚከተሉት ረጅም ለሆነው ጊዜ ይዞ የማቆየት ግዴታ አለበት፡-
  - በንግድ ሕግ ለተወሰነው የሰነድ መያዣ ጊዜ ርዝማኔ፣ ወይም
  - ሰነዶቹ አግባብነት በሚኖራቸው የታክስ ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ለባለሥልጣኑ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ለአምስት ዓመታት፣

6. ስለሠነዶች ....

6.1. መዝገብ የመያዝ ግዴታዎች

- ነገር ግን በአዋጁ መሠረት ለሚደረግ ክርክር ወይም ከላይ ከተመለከተው ጊዜ በፊት ተግባራዊ በሆነ ሕግ መሠረት ለሚደረግ ክርክር ሰነዱ የሚያስፈልግ ሲሆን ታክስ ከፋዩ ሁሉም ክርክሮች እስከሚጠናቀቁ ጊዜ ድረስ ሰነዱን ይዞ የማቆየት ግዴታ አለበት፡፡
- ሰነዱ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ካልቀረበ በባለሥልጣኑ በጹሁፍ በሚሰጥ ማስታወቂያ በሚወሰነው ጊዜ ውስጥ ሰነዱ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ባለው ተርጓሚ በታክስ ከፋዩ ወጪ ወደ አማርኛ ወይም ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉሞ እንዲቀርብ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩን ሊያዘው ይችላል፡፡
- በተጨማሪም ሚኒስትሩ በሚያወጣው የዋጋ ማሸጋገሪያ መመሪያ ሰነድ አያያዝን በተመለከተ የተደነገጉት ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

6. ስለሠነዶች ....

6.2. ሰነዶችን ስለመመርመር

- በታክስ ሕግ መሰረት ሰነዶችን እንዲይዝ የሚገደድ ታክስ ከፋይ በንግድ ህግ በተወሰነው የሰነድ መያዢያ ጊዜ ወይም
- ሰነዶች አግባብነት በሚኖራቸው የታክስ ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ለባለስልጣኑ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባለው **አምስት አመታት** በማንኛውም ምክንያታዊ ጊዜ ውስጥ ሰነዶቹን ለባለሥልጣኑ ምርመራ ዝግጁ የማድረግ ግዴታ አለበት።

6. ስለሠነዶች ....

6.3. ደረሰኞች

ባለሥልጣኑ ለዚህ አፈጻጸም የሚያግዙ መመሪያዎችን የሚያወጣው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

- የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ደረሰኞች ከማሳተሙ በፊት የእነዚህን ደረሰኞች ዓይነት እና ብዛት በባለሥልጣኑ ማስመዝገብ አለበት።
- ማንኛውም የህትመት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ደረሰኞችን ለማሳተም ከታክስ ከፋዩ ጥያቄ ሲቀርብለት ደረሰኞቹን ከማተሙ በፊት የእነዚህ ደረሰኞች ዓይነት እና መጠን በባለሥልጣኑ የተመዘገቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።
- ማንኛውም የሂሣብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ለሚያከናውነው ግብይት ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት።

6.4. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች

- የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪዎችን የሚመለከት ባወጣው ደንብ መሰረት የሚከተሉትን ጉዳዮችን ደንግጓል፡-
  - ➢ ታክስ ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ እንዳለባቸው፣
  - ➢ ታክስ ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የሚጠቀሙበትን ሁኔታዎች፣
  - ➢ በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ታትሞ የሚወጣው ደረሰኝ ሊይዛቸው ስለሚገባ መረጃዎች፣
  - ➢ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው ተፈላጊ ባህሪያት፣
  - ➢ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አቅራቢዎች የሚያቀርቧቸው መሣሪያዎች እውቅና እንዲያገኙ መከተል ስለሚገባቸው ስነ-ሥርዓት እና አቅራቢዎቹ ስላለባቸው ግዴታ፣
  - ➢ ለታክስ ከፋይ የተሸጠን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ስለሚመዘገብበት ሁኔታ፣

6. ስለሠነዶች....

6.4. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች

- ለዚህ አፈጻጸም ሲባል "የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሳሪያ"፣ "የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ" እና "የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ" ምን ማለት እንደሆኑ እንደሚከተለው ይገለፃሉ፡-
  - **"የጥሬ ገንዘብ መዝገቢያ መሳሪያ"** ማለት በሽያጭ መደበኛ ደረሰኝ ፋንታ የዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ሽያጭ የሚመዘግብና ለማንበብ ብቻ የሚቻል ማስታወሻን የሚያከማች በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ፕሮግራም የሚደረግ ቺፕ የተገጠመበት በሰርኪዩት የተጋገረ ፕሮግራም የሚጠቀም መሣሪያ ነው፡፡
  - **"የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ"** ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያን የሚተካ ኮምፒዩተራይዝድ የሆነ መሣሪያ ሲሆን፣ የደንበኞችን ትዕዛዝ፣ የትዕዛዙን አፈጻጸምና ሂደትና የዴቢትና ክሬዲት ካርድ ሂሳብን የመመዝገብና የመከታተል፣ በክምችት ያለን እቃ የመቆጣጠርና የመሳሰሉትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል ተጨማሪ አቅም ያለው መሣሪያ ነው፡፡
  - **"የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ"** ማለት የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም የሽያጭ ነቁጣ መሣሪያ ነው፡፡

7. የታክስ ማስታወቂያዎች

7.1. የታክስ ማስታወቂያዎችን ስለማቅረብ

- በታክስ ሕግ የታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታ የተጣለበት ሰው ማስታወቂያውን በፀደቀው ቅጽ እና በአዋጅ ድንጋጌ እና በደንብ በተመለከተው አኳሃን ማቅረብ አለበት።
- ማንኛውም ታክስ ከፋይ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ፡-
  - ➢ አስቀድሞ ለባለሥለጣኑ ያቀረበውን የታክስ ማስታወቂያ የሚያሟላ የታክስ ማስታወቂያ፣ ወይም
  - ➢ ባለሥልጣኑ በሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ የተመለከቱ መረጃዎችን የያዘ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት።

7. የታክስ ማስታወቂያዎች ....

7.1. የታክስ ማስታወቂያዎችን ስለማቅረብ...

- ቀደም ሲል የቀረበው የታክስ ማስታወቂያ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከሆነ ከላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡
- ባለሥልጣኑ በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ከፋዩ ስም በቀረበ የታክስ ማስታወቂያ አይገደድም፡፡ ስለሆነም ባለሥልጣኑ ባገኘው ማንኛውም አስተማማኝ እና ሊረጋገጥ የሚችል መረጃ ላይ በመመሥረት ታክስ ከፋዩ መክፈል ያለበትን የታክስ መጠን ሊወስን ይችላል፡፡
- የኤሌክትሮኒክስ የታክስ ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ታክስ ከፋይ በሚያቀርበው የታክስ ማስታወቂያ ላይ መፈረም የሚኖርበት ሲሆን የታክስ ማስታወቂያውም፣ ማስታወቂያው እና ተያያዥ ሰነዶችም የተሟሉና ትክክለኛ መሆናቸውን ታክስ ከፋዩ የሚያረጋግጥበትን መግለጫ መያዝ አለበት፡፡

7. የታክስ ማስታወቂያዎች....

7.1. የታክስ ማስታወቂያዎችን ስለማቅረብ...

- ታክስ ከፋዩ፡-
  - ግለሰብ ካልሆነ፣
  - ችሎታ የሌለው ግለሰብ ከሆነ፣ ወይም
  - የታክስ ማስታወቂያውን በሌላ ምክንያት ለመፈረም የማይችል ግለሰብ ሲሆንና ለታክስ ወኪሉ ወይም ለታክስ እንደራሴው በጽሑፍ የውክልና ሥልጣን የሰጠው ከሆነ፣ የታክስ ከፋዩ የታክስ ወኪል ወይም የታክስ እንደራሴው የታክስ ማስታወቂያውን ሊፈርም እና የማረጋገጫ መግለጫ ሊሰጥ ይችላል፡፡
- የታክስ ማስታወቂያው በታክስ ከፋዩ የታክስ ወኪል ወይም በታክስ እንደራሴው የተፈረመ ሲሆን ታክስ ከፋዩ የማስታወቂያውን ይዘት እንደሚያውቅ እና ስለማስታወቂያው የተሟላ እና ትክክለኛ ስለመሆኑ ማረጋገጫ እንደሰጠ ይቆጠራል፡፡

7. የታክስ ማስታወቂያዎች....

7.2. የታክስ ወኪል ስለሚሰጠው የታክስ ማስታወቂያ ማረጋገጫ

- የታክስ ከፋይን የታክስ ማስታወቂያ የሚያዘጋጅ ወይም በታክስ ማስታወቂያ ዝግጅት ድጋፍ የሚያደርግ የታክስ ወኪል የታክስ ከፋዩን ሰነዶች መመርመሩን እና እስከሚያውቀው ድረስ የታክስ ማስታወቂያውና ተያያዥ ሰነዶች የታክስ ማታወቂያው የሚመለከታቸውን መረጃዎች እና ግብይቶች በትክክል የሚያሳዩ መሆኑን የሚያረጋግጥ በፀደቀው ቅጽ መሠረት የተዘጋጀ የምስክር ወረቀት ለታክስ ከፋዩ መስጠት አለበት።
- የታክስ ከፋይን የታክስ ማስታወቂያ የሚያዘጋጅ ወይም በታክስ ማስታወቂያ ዝግጅት ድጋፍ የሚያደርግ የታክስ ወኪል ከታክስ ማስታወቂያው ጋር በተገናኘ ለታክስ ከፋዩ የምስክር ወረቀት የሰጠ ወይም የምስክር ወረቀቱን ያልሰጠበትን ምክንያት የያዘ የጽሁፍ መግለጫ የሰጠ መሆኑን በታክስ ማስታወቂያው ላይ መግለጽ ይኖርበታል።

7. የታክስ ማስታወቂያዎች....

7.3. የታክስ ማስታወቂያዎች አስቀድሞ ስለማቅረብ

- ሥራውን ያቋረጠ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ሥራውን ያቋረጠ መሆኑን ሥራውን ካቆመበት ቀን ጀምሮ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
- ታክስ ከፋይ ሥራውን ባቆመ በ60 (ስልሳ) ቀናት ውስጥ ወይም ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ በሚሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ በሚወስነው ከዚያ ባነሰ ጊዜ ውስጥ፡
  - ታክስ ከፋዩ ሥራውን ላቆመበት የታክስ ጊዜ ወይም የታክስ ማስታወቂያ ጊዜው ላልደረሰ ከዚያ በፊት ለነበረ የታክስ ጊዜ የቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ፣ እና
  - በቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያው መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ታክስ መክፈል አለበት፡፡
- ማንኛውም ታክስ ከፋይ ከኢትዮጵያ ሊወጣ ከሆነና የታክስ ከፋዩ ከኢትዮጵያ መውጣት በጊዜያዊነት አለመሆኑ የሚገመት ከሆነ ታክስ ከፋዩ ከኢትዮጵያ ከመውጣቱ በፊት፡
  - የወቅቱን የታክስ ማስታወቂያ እና ከኢትዮጵያ በሚወጣበት ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ የማቅረቢያ ጊዜው ላልደረሰው ከዚያ በፊት ለነበረው የታክስ ጊዜ የቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ፣ እና
  - በቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያው መሠረት መከፈል የሚገባውን ታክስ መክፈል ወይም ታክሱ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለባለሥልጣኑ አጥጋቢ በሆነ አኳሃን ማመቻቸት አለበት፡፡

7. የታክስ ማስታወቂያዎች ....

7.3. የታክስ ማስታወቂያዎች አስቀድሞ ስለማቅረብ ...

- በማንኛውም የታክስ ጊዜ ታክስ ከፋዩ የታክስ ጊዜውን የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ በሚገባው ጊዜ አያቀርብም ብሎ ማመን የሚያስችል ምክንያት ሲኖረው ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት፡-
  - ታክስ ከፋዩ ወይም የታክስ እንደራሴው የታክስ ጊዜው የታክስ ማስታወቂያ ማቅረቢያ ጊዜ ባይደርስም ባለሥልጣኑ በሰጠው ማስታወቂያ በተመለከተው ጊዜ የቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያ እንዲያቀርብ፣ እና
  - በቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያው የተመለከተውን ታክስ ባለሥልጣኑ በሰጠው ማስታወቂያ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል፣ ሊያዝ ይችላል።
- ታክስ ከፋዩ ከአንድ የታክስ ዓይነት በላይ የሚመለከተው ከሆነ ለእያንዳንዱ ታክስ በተናጠል ተፈጻሚ ይሆናል።
- **"ሥራ"** ማለት ንግድ ወይም ማንኛውም በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ የሚከፈልበትን ገቢ የሚያስገኝ ሌላ ሥራ ሲሆን የመጨረሻ ታክስ ሆኖ ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ለባለሥልጣኑ የሚተላለፍ ታክስ የሚከፈልበትን ገቢ የሚያስገኝ ሥራን አይጨምርም።

7. የታክስ ማስታወቂያዎች ....

7.4. በአግባቡ የቀረበ የታክስ ማስታወቂያ

- በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ከፋዩ ስም ቀርቧል የተባለ የታክስ ማስታወቂያ በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ከፋዩ ፈቃድ እንደቀረበ ይቆጠራል፡፡

8. የታክስ ስሌቶች

8.1. በታክስ ከፋዩ ስለሚዘጋጅ የታክስ ስሌት

- በፀደቀው ቅጽ መሠረት ለአንድ የታክስ ጊዜ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ያቀረበ የራሱን ታክስ ስሌት የሚያዘጋጅ ታክስ ከፋይ በታክስ ስሌት ማስታወቂያው የገለፀው መጠን ለማንኛውም የታክስ ማስታወቂያው ተፈጻሚ ለሚሆንበት የታክስ ጊዜ ዜሮን ጨምሮ ሊከፈል የሚገባውን የታክስ መጠን ስሌት እንዳቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡
- በፀደቀው ቅጽ መሠረት ለአንድ የታክስ ጊዜ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ያቀረበ የራሱን የታክስ ስሌት የሚያዘጋጅ በገቢ ግብር አዋጅ ሠንጠረዥ “ለ” ወይም “ሐ” መሠረት ታክስ የሚከፈልበትን ገቢ የሚያገኝ ታክስ ከፋይ በዚሁ የታክስ ጊዜ ኪሣራ የገጠመው እንደሆነ በታክስ ስሌት ማስታወቂያው የገለፀው የኪሣራ መጠን ለማንኛውም የታክስ ማስታወቂያው ተፈጻሚ ለሚሆንበት የታክስ ጊዜ ያጋጠመውን የኪሣራ ስሌት እንዳቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

8. የታክስ ስሌቶች …

8.1. በታክስ ከፋዩ ስለሚዘጋጅ የታክስ ስሌት …

- ለአንድ የታክስ ጊዜ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ያቀረበ የራሱን የታክስ ስሌት የሚያዘጋጅ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ታክስ ከፋይ፣ በዚሁ የታክስ ጊዜ በግብዓት ላይ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቅላላ መጠን የተጨማሪ እሴት ታክስ ከሚከፈልበት ሽያጭ ላይ ከሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቅላላ መጠን የበለጠ እንደሆነ፣ በታክስ ስሌት ማስታወቂያው የገለፀው የታክስ መጠን ለማንኛውም የታክስ ማስታወቂያው ተፈጻሚ ለሚሆንበት የታክስ ጊዜ ታክስ ከሚከፈልበት ሽያጭ ላይ ከሰበሰበው ታክስ በላይ የግብዓት ታክስ መክፈሉን የሚገልጽ የስሌት ማስታወቂያ እንዳቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል።
- የታክስ ማስታወቂያ፡- ቅጹ በባለሥልጣኑ አስቀድሞ የተሞላ መረጃ የያዘ ቢሆንም፣ እንዲሁም ሊከፈል የሚገባው ታክስ መረጃ በቅጹ ውስጥ እየተሞላ ሳለ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የተሰላ ቢሆንም፣ በፀደቀው ቅጽ መሠረት በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ተሞልቶ በታክስ ከፋይ የቀረበ የታክስ ማስታወቂያ የራሱን የታክስ ስሌት በሚያዘጋጅ ታክስ ከፋይ እንደቀረበ ተደርጎ ይቆጠራል።

8. የታክስ ስሌቶች....

8.2. በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት

- ማንኛውም ታክስ ከፋይ በማንኛውም የታክስ ጊዜ ማቅረብ የሚገባውን የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ እንደሆነ ባለሥልጣኑ በማንኛውም ጊዜ የሚያገኘውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ለታክስ ጊዜው ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ በግምት ማስላት የሚችል ሲሆን የግምት ስሌቱ የሚከተሉትን ይመለከታል፡-
  - ➢ የገቢ ግብር አዋጅ ሠንጠረዥ "ለ" ና "ሐ" ኪሰራን በሚመለከት የታክስ ጊዜውን የኪሳራ መጠን፣
  - ➢ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሠረት በግብዓት ላይ በብልጫ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስን በሚመለከት ለታክስ ጊዜው በግብዓት ላይ በብልጫ የተከፈለውን የታክስ መጠን፣
  - ➢ በሌላ ማንኛውም ሁኔታ ዜሮ መጠንን ጨምሮ በታክስ ጊዜው ሊከፈል የሚገባውን የታክስ መጠን፡፡

8. የታክስ ስሌቶች....

8.2. በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት...

- ባለሥልጣኑ ታክሱን በግምት ከወሰነ በግምት ለተሰላው ታክስ ከፋይ የሚከተሉትን ዝርዝር ነጥቦች ያካተተ የታክስ ግምት ስሌት ማስታወቂያ መስጠት አለበት፡-
  - እንደሁኔታው የተሰላውን የታክስ መጠን፣ ወደፊት የሚሸጋገር የኪሣራ ወይም በበልጫ የተከፈለን የግብዓት ታክስ መጠን፣
  - በተሰላው ታክስ ላይ ሊከፈል የሚገባ የቅጣት መጠን ካለ፣
  - በተሰላው የታክስ መጠን ላይ ሊከፈል የሚገባ የዘገየ ክፍያ ወለድ መጠን ካለ፣
  - የታክስ ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ጊዜ፤
  - ማስታወቂያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ታክሱ፣ ቅጣቱ እና ወለዱ የሚከፈልበትን ቀን፤
  - ቅሬታ ማቅረብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ጨምሮ በታክስ ግምት ስሌቱ ላይ ቅሬታውን የሚያቀርብበትን አኳሃን፣

8. የታክስ ስሌቶች....

8.2. በግምት የሚከናወን የታክስ ስሌት...

- የሚሰጠው የታክስ ግምት ስሌት ማስታወቂያ ታክሱን በሚጥለው የታክስ ሕግ መሠረት በተዘጋጀው የታክስ ግምት ስሌት ሊከፈል የሚገባው ታክስ የሚከፈልበትን ጊዜ ሊለውጥ የማይችል ሲሆን፣ የታክስ ክፍያው በመዘግየቱ ምክንያት የሚጣል ቅጣትና ወለድ መታሰብ የሚጀምሩት ከመጀመሪያው የመክፈያ ጊዜ አንስቶ ይሆናል፡፡
- ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው በታክስ ስሌት ለሚሰበሰብ ታክስ ብቻ ነው፡፡
- በባለሥልጣኑ የተዘጋጀ የታክስ ግምት ስሌት የደረሰው ማንኛውም ታክስ ከፋይ የግምት ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታውን አያስቀርም፡፡
- በባለሥልጣኑ የተዘጋጀ የታክስ ግምት ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከደረሰው በኋላ ለዚያ የታክስ ጊዜ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የታክስ ማስታወቂያ ለታክስ ጊዜው እንደቀረበ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ሆኖ አይቆጠርም፡፡
- ባለሥልጣኑ በማንኛውም ጊዜ በግምት ላይ የተመሠረተ የታክስ ስሌት ሊያዘጋጅ ይችላል እንዲሁም አፈጻጸሙን የሚያግዙ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

8. የታክስ ስሌቶች ....

8.3. የስጋት የታክስ ስሌት

- ባለሥልጣኑ የታክስ ማስታወቂያዎች አስቀድሞ የሚቀርብበት ወይም በፋይናንስ ተቋማት የተቀመጠ ገንዘብ እና ንብረት ይዞ ማቆየት የሚጠበቅበት ሁኔታዎች ሢኖር በአንድ የታክስ ጊዜ ማንኛውም ታክስ ከፋይ መክፈል ለሚገባው ታክስ በሚያገኘው ማስረጃ ላይ በመመሥረት የስጋት ታክስ ስሌት ሊያዘጋጅ ይችላል።
- ይህ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለው፡- ታክስ ከፋዩ ለታክስ ጊዜው የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ እንደሆነ፣ እና ታክሱ በታክስ ስሌት የሚሰበሰብ ሲሆን ብቻ ነው።
- ይሄ የስጋት ታክስ ስሌት:-
  - ታክስ ከፋዩ ለታክስ ጊዜው የታክስ ማስታወቂያ የሚያቀርብበት ቀን ከመድረሱ በፊት ሊዘጋጅ ይችላል፣
  - በሚዘጋጅበት ጊዜ ፀንቶ ባለ ሕግ መሠረት መዘጋጀት አለበት።

8. የታክስ ስሌቶች....

8.3. የስጋት የታክስ ስሌት...

- ባለሥልጣኑ የስጋት ታክስ ስሌት ለተዘጋጀለት ታክስ ከፋይ የሚከተሉትን ዝርዝር ነጥቦች ያካተተ የስጋት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ በጽሑፍ መስጠት አለበት፡-
  - የተሳለውን የታክስ መጠን፤
  - በተሰላው የታክስ መጠን ላይ የሚከፈል ቅጣት ካለ፣
  - የታክስ ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ጊዜ፣
  - ታክሱና ቅጣቱ የሚከፈልበትን ጊዜ፣ ይህ ጊዜ የታክሱ የመክፈያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ሊሆን ይችላል፣
  - ቅሬታ ማቅረብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ጨምሮ በስጋት ታክስ ስሌቱ ላይ ቅሬታውን የሚያቀርብበትን አኳሃን፣

8.3. የስጋት የታክስ ስሌት...

- ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ በሚሰጠው የስጋት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ታክሱ እና ቅጣቱ ወዲያውኑ እንዲከፈሉ ሊያዝ ይችላል፡፡
- በባለሥልጣኑ የተዘጋጀ የስጋት ታክስ ስሌት የደረሰው ማንኛውም ታክስ ከፋይ የስጋት ታክስ ስሌቱ የሚመለከተውን የታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታውን አያስቀርም፡፡
- ታክስ ከፋዩ በአንድ የታክስ ጊዜ መክፈል ያለበትን ታክስ በሙሉ ማስላት እንዲቻል የስጋት ታክስ ስሌት ውሳኔው የተሻሻሉ የታክስ ስሌቶች በሚሰሉበት አኳኋን ሊሻሻል ይችላል፡፡
- የስጋት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከደረሰው በኋላ ለዚያ የታክስ ጊዜ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የታክስ ማስታወቂያ ለታክስ ጊዜው እንደቀረበ በታክስ ከፋዩ የተዘጋጀ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ አይቆጠርም፡፡

8. የታክስ ስሌቶች....

8.4. የተሻሻሉ የታክስ ስሌቶች እና የይርጋ ጊዜ ገደብ

ባለሥልጣኑ ማንኛውንም የታክስ ስሌት ፡-

- የገቢ ግብር አዋጅ ሠንጠረዥ "ለ" ወይም "ሐ"ን በተመለከተ የታክስ ከፋዩ ኪሳራ ለታክስ ጊዜው በትክክል የተሰላ መሆኑን፤
- በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሠረት በብልጫ የተከፈለ የግብዓት ተጨማሪ እሴት ታክስ መጠንን በተመለከተ ታክስ ከፋዩ በታክስ ጊዜው በብልጫ የከፈለው የግብዓት ተጨማሪ እሴት ታክስ በትክክል የተሰላ መሆኑን፣
- በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ታክስ ከፋዩ ዜሮ መጠንን ጨምሮ ለታክስ ጊዜው መክፈል የሚገባው የታክስ መጠን በትክክል የተሰላ መሆኑን፣ ለማረጋገጥ በሚያገኘው ማስረጃ መሠረት ማንኛውንም የታክስ ስሌት በመለወጥ፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር ሊያሻሽል ይችላል።

8. የታክስ ስሌቶች....

8.4. የተሻሻሉ የታክስ ስሌቶች እና የይርጋ ጊዜ ገደብ...

- ባለሥልጣኑ ማንኛውንም የታክስ ስሌት፡-

ሀ) የታክስ ባለስልጣኑ የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያገኘ እንደሆነ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያውን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 10 (አስር) ዓመት ውስጥ፤ ወይም

ለ) በሌላ በማናቸውም ሁኔታ በሚከተለው የይርጋ ጊዜ ውስጥ ፡-

- ✓ ታክስ ከፋዩ በራሱ የሚያሰላው የታክስ ስሌት ሲሆን ታክስ ከፋዩ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያውን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 5(አምስት) ዓመት ውስጥ፣
- ✓ ለሌላ ማንኛውም የታክስ ስሌት ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 5(አምስት) ዓመት ውስጥ ሊያሻሽል ይችላል።

8. የታክስ ስሌቶች....

8.4. የተሻሻሉ የታክስ ስሌቶች እና የይርጋ ጊዜ ገደብ...

- **“የታክስ ማጭበርበር”** ማለት ታክስን ለመሰወር ወይም ህጋዊ ያልሆነ የታክስ ጥቅም ለማግኘት ሲባል የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም ወይም አለመፈጸም ነው፤

ሀ) ሐሰተኛ የሂሳብ መዝገቦችን፣ ሰነዶችን፣ ደረሰኞችን ወይም ሌሎች ሰነዶችን ማቅረብ፣

ለ) ገቢን፣ ግብይትን ወይም ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ መደበቅ፣

ሐ) ሐሰተኛ ደረሰኞችን ማዘጋጀት ወይም መጠቀም፣

መ) ሐሰተኛ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ

ሠ) ሰነዶችን ማጥፋት፣ መቀየር፣ መደበቅ፣

ረ) የተለያዩ የሂሳብ መዝገቦችን ወይም የሂሳብ ሰነዶችን ለታክስ ባለስልጣኑ እና ለተለያዩ አካላት ማቅረብ፤

ሰ) ሐሰተኛ የተቀናሽ ወጪዎችን፣ የግብር ወይም የታክስ ነፃ መብት፣ የተመላሽን፣ ወይም የማካካሻ ጥያቄን ማቅረብ፤

ሸ) የታክስ ባለስልጣኑን ለማሳሳት ወይም ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የታክስ ግዴታን ለመቀነስ ማናቸውንም ሌሎች ድርጊቶች መፈጸም።

8. የታክስ ስሌቶች....

8.4. የተሻሻሉ የታክስ ስሌቶች እና የይርጋ ጊዜ ገደብ...

- ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ የሰጠውን የታክስ ስሌት ማሻሻያ ማስታወቂያ ከሚከተሉት ሁኔታዎች ዘግይቶ በተፈጸመው ጊዜ እንደገና ሊያሻሽል ይችላል፡፡
  - ለመጀመሪያው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ታክስ ከፋዩ **የራስ ታክስ ስሌት** ማስታወቂያውን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር **5 ዓመት** ጊዜ ውስጥ ወይም
  - ለሌላ ማንኛውም የታክስ ስሌት ለታክስ ከፋዩ **የታክስ ስሌት ማስታወቂያ** ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር **5 ዓመት** ውስጥ ወይም
  - ባለሥልጣኑ የተሻሻለውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከሰጠው በኋላ ባለው **የአንድ ዓመት** ጊዜ ውስጥ፡፡
- ባለሥልጣኑ የተሻሻለውን የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከሰጠው በኋላ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የታክስ ስሌት ማሻሻያ ማስታወቂያውን እንደገና የሚያሻሽል ሂደት ተፈጻሚ በሚሆንበት በማናቸውም ሁኔታ ባለሥልጣኑ የሚያደርገው ተጨማሪ ማሻሻያ መጀመሪያ በተሻሻለው የታክስ ስሌት ላይ በተደረጉት ለውጦች፣ ቅናሾች ወይም ጭማሪዎች ላይ ብቻ የተገደበ ይሆናል፡፡

8.4. የተሻሻሉ የታክስ ስሌቶች እና የይርጋ ጊዜ ገደብ...

- ባለሥልጣኑ የተሻሻለውን የታክስ ስሌት በተመለከተ የሚከተሉትን ነጥቦች ያካተተ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ መስጠት አለበት፡-
    - ማሻሻያ የተደረገበትን የመጀመሪያ የታክስ ስሌት እና ማሻሻያ ማድረግ ያስፈለገበትን ምክንያቶች የያዘ መግለጫ፣
    - እንደሁኔታው የተሰላውን የታክስ መጠን፣ ወደፊት የሚሸጋገር የኪሣራ ወይም በበልጫ የተከፈለን የግብዓት ታክስ መጠን፣
    - በተሻሻለ የታክስ ስሌት ላይ ሊከፈል የሚገባ የቅጣት መጠን ካለ፣
    - በተሻሻለው የታክስ ስሌት ላይ ሊከፈል የሚገባ የዘገየ ክፍያ ወለድ መጠን ካለ፣
    - የተሻሻላ የታክስ ስሌት የሚመለከተውን የታክስ ጊዜ፣
    - ማስታወቂያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ከ30 (ሰላሳ) ቀናት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ በተሻሻለው የታክስ ስሌት መሠረት መከፈል ያለበትን ተጨማሪ ታክስ፣ ቅጣት እና ወለድ የሚከፈልበትን ቀን፣
    - ቅሬታ ማቅረብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ጨምሮ በተሻሻለው የታክስ ስሌት ላይ ቅሬታውን የሚያቀርብበትን አኳሃን፣

8. የታክስ ስሌቶች….

8.5. ታክስ ከፋዩ ራሱ ያዘጋጀው የታክስ ስሌት እንዲሻሻል ስለሚቀርብ ማመልከቻ

- የራሱን የታክስ ስሌት ያዘጋጀ ታክስ ከፋይ ያቀረበውን በራስ የተዘጋጀ የታክስ ማስታወቂያ ባለሥልጣኑ እንዲያሻሽልለት ለባለሥልጣኑ ሊያመለክት ይችላል።
- በዚህ መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ፣
  - ➢ ታክስ ከፋዩ ራሱ አዘጋጅቶ ባቀረበው የታክስ ማስታወቂያ ላይ ሊደረጉ ይገባል ብሎ የሚያምንባቸውን ማሻሻያዎችን እና ማሻሻያዎቹን ማድረግ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያቶች መግለጽ፣ እና
  - ➢ ታክስ ከፋዩ የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያውን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር አምስት ዓመት /5/ ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል።
- በዚህ ድንጋጌ መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት ማመልከቻው በቀረበለት በ120 (አንድ መቶ ሃያ) ቀናት ውስጥ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በታክስ ከፋዩ ተዘጋጅቶ የቀረበው የታክስ ስሌት እንዲሻሻል መወሰን ወይም ማመልከቻውን ውድቅ ማድረግ አለበት።

8. የታክስ ስሌቶች....

8.5. ታክስ ከፋዩ ራሱ ያዘጋጀው የታክስ ስሌት እንዲሻሻል ስለሚቀርብ ማመልከቻ ...

- ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ ራሱ ያቀረበው የታክስ ስሌት እንዲሻሻል የወሰነ እንደሆነ፣
  - የታክስ ስሌት ማሻሻያው ባለስልጣኑ የታክስ ከፋዩ ኪሣራ በትክክል የተሰላ መሆኑን፣ ታክስ ከፋዩ በታክስ ጊዜው የከፈለው የግብዓት ተጨማሪ እሴት ታክስ በትክክል የተሰላ መሆኑን እና በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ታክስ ከፋዩ ዜሮ መጠንን ጨምሮ ለታክስ ጊዜው መክፈል የሚገባውን የታክስ መጠን በትክክል የተሰላ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚያገኘው ማስረጃ መሰረት ማንኛውንም የመጀመሪያ የታክስ ስሌት ተብሎ የሚጠቀሰውን በመለወጥ፣ በመቀነስ፣ ወይም በመጨመር ሊያሻሽል ይችላል።
  - የተሻሻለው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ቀጥሎ የተመለከቱትን መረጃዎች የያዘ መግለጫ ለታክስ ከፋዩ እንዲደርሰው መደረግ አለበት፡-
    - ✓ ማሻሻያ የተደረገበትን የመጀመሪያ የታክስ ስሌት እና ማሻሻያ ማድረግ ያስፈለገበትን ምክንያቶች የያዘ መግለጫ፣
    - ✓ እንደሁኔታው የተሰላውን የታክስ መጠን፣ ወደፊት የሚሸጋገር የኪሣራ ወይም በበልጫ የተከፈለን የግብዓት ታክስ መጠን፣

8. የታክስ ስሌቶች....

8.5. ታክስ ከፋዩ ራሱ ያዘጋጀው የታክስ ስሌት እንዲሻሻል ስለሚቀርብ ማመልከቻ ...

- ✓ በተሻሻለ የታክስ ስሌት ላይ ሊከፈል የሚገባ የቅጣት መጠን ካለ፣
- ✓ በተሻሻለው የታክስ ስሌት ላይ ሊከፈል የሚገባ የዘገየ ክፍያ ወለድ መጠን ካለ፣
- ✓ የተሻሻላ የታክስ ስሌት የሚመለከተውን የታክስ ጊዜ፣
- ✓ ማስታወቂያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ከ30 (ሰላሳ) ቀናት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ በተሻሻለው የታክስ ስሌት መሠረት መከፈል ያለበትን ተጨማሪ ታክስ፣ ቅጣት እና ወለድ የሚከፈልበትን ቀን፣
- ✓ ቅሬታ ማቅረብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ጨምሮ በተሻሻለው የታክስ ስሌት ላይ ቅሬታውን የሚያቀርብበትን አኳሃን፣ ባለሥልጣኑ በዚህ መሠረት የሚቀርበውን ማመልከቻ ያልተቀበለው እንደሆነ ውሳኔውን ለታክስ ከፋዩ በጽሁፍ ያሳውቃል።

9.ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመሰብሰብና ማስከፈል

9.1. ታክስ ለመንግሥት የሚከፈል ዕዳ ስለመሆኑ

- በታክስ ሕግ መሠረት በታክስ ከፋዩ ሊከፈል የሚገባውና የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ታክስ ለመንግሥት የሚከፈል ዕዳ ስለሆነ ለባለሥልጣኑ መከፈል አለበት።
- በኤሌክትሮኒክስ አከፋፈል ዘዴ ታክስ እንዲከፍል በባለሥልጣኑ የተጠየቀ ታክስ ከፋይ ባለሥልጣኑ ሌላ የአከፋፈል ዘዴ እንዲጠቀም በጽሑፍ ካልፈቀደለት በስተቀር ክፍያውን የሚፈጽመው በኤሌክትሮኒክስ አከፋፈል ዘዴ ይሆናል።
- ታክስ ከፋዩ ታክሱን መክፈል ባለበት ጊዜ ካልከፈለ ባለሥልጣኑ ያልተከፈለውን ታክስ ለማስከፈል በሚወስደው እርምጃ ምክንያት ለሚያወጣው ማንኛውም ወጪ ኃላፊ ይሆናል።

9.ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመሰብሰብና ማስከፈል

9.2. በሁለተኛ ደረጃ የሚመጡ ኃላፊነቶች እና ታክስን ለማስከፈል የሚደረጉ ወጪዎች

- ባለሥልጣኑ የሁለተኛ ደረጃ ኃላፊነት ላለበት ወይም ታክስን ለማስከፈል የተደረገን ወጪ መክፈል ላለበት ማንኛውም ሰው መክፈል ያለበትን የገንዘብ መጠን እና ክፍያው የሚፈጸምበትን ቀን የሚገልጽ ማስታወቂያ ይሰጣል፡፡
- የሁለተኛ ደረጃ ኃላፊነት ባለበት ሰው የተከፈለ ታክስ ይኸው ኃላፊነት ከሚመለከተው የታክስ ከፋዩ የመጀመሪያ የታክስ ኃላፊነት ጋር ይካካሳል፡፡

9.ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመሰብሰብና ማስከፈል

9.3. የታክስ መክፈያ ጊዜን ስለማራዘም

- የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ታክስ የመክፈያ ጊዜው እንዲራዘም ለባለሥልጣኑ የጽሑፍ ማመልከቻ ሊቀርብ ይችላል፡፡
- ማመልከቻ በሚቀርብበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በቂ ምክንያት መኖሩን ካረጋገጠ
    - ለታክስ ከፋዩ የታክስ መክፈያ ጊዜውን ሊያራዝምለት ወይም
    - ባለሥልጣኑ በሚወሰነው መሠረት ታክሱን በመከፋፈል በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል ሊያደርገው ይችላል፡፡
- ለቀረበው ማመልከቻ የሰጠውን ውሳኔ የሚገለጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ይሰጠዋል፡፡
- ታክሱን በመከፋፈል በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ የአንድን ጊዜ ክፍያ ካልከፈለ ታክስ ከፋዩ ክፍያውን ባቆመበት ጊዜ ያለውን ቀሪ ክፍያ በሙሉ እንዲከፍል ባለሥልጣኑ ወዲያውኑ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡
- በዘገየው ክፍያ ላይ ከመጀመሪያ የታክስ መክፈያ ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ወለድ የመክፈል ግዴታው አለበት፡፡

9.4. በታክስ እና ለሦስተኛ ወገን በሚሰጥ የክፍያ ትዕዛዝ በሚከፈል ገንዘብ ላይ ስለሚኖር የቅድሚያ መብት……

- ይህን ገንዘብ ባለዕዳ የሆነ፣ የያዘ፣ የተረከበ ወይም ቀንሶ የሚያስቀር ሰው ገንዘቡ የመንግሥት ባለአደራ በመሆን የሚይዝ ስለሆነ ይህ ሰው ሲከስር ወይም ንብረቱ ሲጣራ የመንግሥት ባለአደራ በመሆን የያዘው ገንዘብ፡-
  - በንብረት ማጣራቱ ሂደት ወይም በኪሳራው የጠቅላላ ንብረቱ አካል ተደርጎ አይወሰድም፣ እንዲሁም
  - ምንም ዓይነት የንብረት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት ለባለሥልጣኑ መከፈል አለበት፡፡
- በሌላ ማንኛውም ሕግ በተለየ አኳን የተደነገገ ቢኖርም ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ታክስ፡-
  - ከማንኛውም ሰው ለሚፈለግ ማንኛውም ዕዳ ወይም ኃላፊነት ማስፈጸሚያ ሊከበር አይችልም፡፡
  - ታክሱ ተይዞ ቀሪ ከሚደረግበት ክፍያ ላይ ከሚፈለጉ እዳዎች ሁሉ የመጀመሪያው ይሆናል፡፡ እንዲሁም
  - በማናቸውም ሕግ ወይም የፍርድ ቤት ትእዛዝ መሠረት ከክፍያው ላይ ከሚቀነስ ማንኛውም የገንዘብ ክፍያ ቅድሚያ ይኖረዋል፡፡

9.ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመሰብሰብና ማስከፈል

9.5. የአከፋፈል ቅደም ተከተል

- ታክስ ከፋዩ የፈፀመው ክፍያ መክፈል ከሚገባው ጠቅላላ የታክስ፣ የቅጣትና የወለድ መጠን ያነሰ በሚሆንበት ጊዜ የተከፈለው ገንዘብ የሚሸፍነው ዕዳ ቅደም ተከተልን በተመለከተ፡-
  - ➢ በመጀመሪያ ዋናውን የታክስ ዕዳ ለመክፈል፤
  - ➢ ቀጥሎ ክፍያ ለዘገየበት የሚከፈል ወለድ፣
  - ➢ ቀሪው ገንዘብ ለቅጣት መክፈያ ይውላል።
- ከአንድ በላይ የታክስ ዕዳ የሚፈለግበት ግብር ከፋይ ክፍያው የሚሸፍነው ዕዳ ቅደም ተከተል ዕዳው በተፈጠረበት ጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት ይሆናል ።

9.6. ለታክስ አከፋፈል የሚቀርብ ዋስትና

- ባለሥልጣኑ የመንግሥትን ገቢ ለመጠበቅ አስፈላጊ መስሎ ሲታየው አስፈላጊ ነው በሚለው መጠንና አኳኋን ታክሱ ከፋዩ ዋስትና እንዲያቀርብ ሊያስገድደው ይችላል። ታክስ ከፋዩ ዋስትና እንዲያቀርብ የሚጠየቀውም፦
  - የመክፈያ ጊዜው ለደረሰ ወይም የመክፈያ ጊዜው ለሚደርስ ታክስ መክፈያ፣ ወይም
  - በታክስ ሕግ መሠረት ተመላሽ ለሚጠይቅ ታክስ ከፋይ ቅድመ-ሁኔታ ይሆናል።
- የሚሰጥ ዋስትና ባለሥልጣኑ የሚጠይቃቸው ተገቢ ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ ዋስትና ሊሰጥ ይችላል።
- ታክስ ከፋዩ ዋስትና የማቅረብ ግዴታ የሚኖርበት ባለሥልጣኑ፦
  - የሚፈለገው የዋስትና መጠን፣
  - ዋስትናው የሚቀርብበትን አኳኋን፣ እና
  - ዋስትናው የሚቀርብበትን ቀን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ የሰጠ እንደሆነ ብቻ ነው።

9.ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመሰብሰብና ማስከፈል

9.7. ስለ ጥበቃ

- ታክስ ከፋዩን በመወከል በታክስ ሕግ መሰረት ለባለሥልጣኑ እንዲከፍል ግዴታ የተጣለበት ሰው እና ማካካሻ ስለሚያገኝበት ሁኔታ፦
- ተፈፃሚ የሚሆንበት ሰው፦
  - ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ታክስ ቀንሶ ለባለሥልጣኑ የከፈለ ሰው፤
  - ለባለሥልጣኑ ታክስ የከፈለ የታክስ እንደራሴ፣
  - ለባለሥልጣኑ ታክስ የከፈለ ተረካቢ፣ ወይም
  - ለሦስተኛ ወገን በሚሰጥ የክፍያ ትዕዛዝ መሠረት ለባለሥልጣኑ ገንዘብ የከፈለ ሰው።
- ታክስ ከፋዩን በመወከል በታክስ ሕግ መሰረት ለባለሥልጣኑ የከፈለው ገንዘብ በታክስ ከፋዩ እንዲተካለት የመጠየቅ መብት አለው።

10. ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

10.1. ለዘገየ ክፍያ የሚከፈል ወለድ

- በታክስ መክፈያ ጊዜው ወይም ከዚያ በፊት ታክሱን ያልከፈለ ታክስ ከፋይ ታክሱ መከፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀበት ቀን ድረስ ባልተከፈለው መጠን ላይ ለዘገየው ክፍያ ወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
- የዘገየ ክፍያ የወለድ መጣኔ በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ መጣኔ ላይ 15% (አሥራ አምስት በመቶ) ተጨምሮበት ይሆናል፡፡
- በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ በዚህ አዋጅ መሠረት ታክስን በመክፈያ ጊዜው ባለመክፈል ከሚጣለው ቅጣት በተጨማሪ ይሆናል፡፡
- በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ በነጠላ ወለድ የሚሰላ ሲሆን የሚታሰበውም በየቀኑ ይሆናል፡፡

10. ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

10.1. ለዘገየ ክፍያ የሚከፈል ወለድ ....

- ታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳ የታክስ ስሌት ማስታወቂያን እስከተሰጠበት ቀን ድረስ መክፈል የሚጠበቅበትን የዘገየ ክፍያ ወለድን ጨምሮ በማስታወቂያው የተመለከተውን የታክስ ዕዳ በሙሉ በማስታወቂያው በተገለጸው የመክፈያ ቀን የከፈለ ከሆነ ማስታወቂያው በተሰጠበት እና ክፍያው በተፈፀመበት መካከል ላለው ጊዜ የዘገየ ክፍያ ወለድ አይታሰብም፡፡
- ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ በሚከፈል ታክስ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ኃላፊነት በሚከፈል ታክስ ላይ የሚታሰብ የዘገየ ክፍያ ወለድ መከፈል ያለበት ይኸው ኃላፊነት ባለበት ሰው ብቻ በመሆኑ ከሌላ ማንኛውም ሰው ሊጠየቅ አይችልም፡፡
- በዘገየ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ ጠቅላላ መጠን ከታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳ ሊበልጥ አይችልም፡፡

10.2. የታክስ ስሌቶችን ስለማስፈጸም

- ታክስ ከፋዩ በዚህ አዋጅ ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ቅሬታ ካለቀረበ ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ የሚሰጠው የታክስ ስሌት የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜው ካበቃበት ቀን ጀምሮ የመጨረሻ እና ተፈጻሚነት ያለው ይሆናል፡፡
- ታክስ ከፋዩ በታክስ ስሌቱ ላይ ቅሬታ ካቀረበ፣ የታክስ ስሌቱ ከሚከተሉት የዘገየው ሁኔታ በተፈጸመበት ጊዜ የመጨረሻ ይሆናል፡-
  - ታክስ ከፋዩ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካለቀረበ፣ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሲጠናቀቅ (30 ቀናት)፣
  - ታክስ ከፋዩ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካቀረበ፣ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚቀርብበት ጊዜ ሲጠናቀቅ (የኮሚሽኑ ውሳኔ በደረሰ 30 ቀናት ውስጥ)፣
  - ታክስ ከፋዩ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካቀረበ፣ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚቀርብበት ጊዜ ሲጠናቀቅ (የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትውሳኔ በደረሰ 30 ቀናት ውስጥ)፣
  - ታክስ ከፋዩ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በታክስ ስሌቱ ላይ ይግባኝ ካቀረበ፣ ፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ፣

10. ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

10.3. በሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ጥያቄ

- በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ ከፋዩ መክፈል የሚገባው የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ታክስ በሙሉ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ባለሥልጣኑ በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የቀደምትነት መብት ይኖረዋል።
- የቀደመ ዋስትና የተሰጠበት መብት ባንኮች ዋስትና የተቀበሉባቸው የገንዘብ ጥያቄዎችና የተቀጣሪዎችን የደመወዝ የቅድሚያ መብት ይጨምራል። ሆኖም
    - ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ በሚከፈል ታክስ፣
    - በተጨማሪ እሴት ታክስ፣
    - በተርንኦቨር ታክስ፣
    - በኤክሳይዝ ታክስ፣ እና
    - ለሦስተኛ ወገን በሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ መሠረት ሊከፈል በሚገባው ገንዘብ፤ ከተመለከቱት ታክሶች ጋር በተገናኘ ተፈጻሚ አይሆንም።

10. ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

10.4. የተረካቢዎች ግዴታዎች

- ማንኛውም ተረካቢ የአንድን ታክስ ከፋይ ሀብት በኢትዮጵያ ውስጥ ተረካቢ ሆኖ ከተሾመ ወይም ሀብቱ በይዞታው ሥር ከገባ ከሁለቱ ከሚቀድመው ጊዜ ጀምሮ ባሉት አሥራ አራት ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።
- ባለሥልጣኑ ሀብቱ በተረካቢው ቁጥጥር ሥር ባለው ታክስ ከፋይ ያልተከፈለውን የታክስ ዕዳ እና ወደፊት የሚከፈለውን የታክስ መጠን በመወሰን የጽሑፍ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ለተረካቢው ማሳወቅ አለበት።
- ተረካቢው
  - ከባለሥልጣኑ አስቀድሞ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር በእጁ የሚገኘውን የታክስ ከፋዩን ሀብት ማስታወቂያ ከባለስልጣኑ ተሰጥቶት የ30 ቀናት ጊዜ ከማለፍ በፊት መሸጥ ወይም በማናቸውም ሁኔታ ማስተላለፍ አይችልም።
  - ከሀብቱ ሽያጭ ገንዘብ ላይ ባለሥልጣኑ የገለጸውን የታክስ መጠን ወይም ባለሥልጣኑ የተስማማበትን የታክስ መጠን ቀንሶ ማስቀመጥ አለበት። እንዲሁም
  - የሀብቱ ባለቤት በሆነው ታክስ ከፋይ መክፈል ላለበት ታክስ ከሀብቱ ሽያጭ ገቢ ተቀንሶ መቀመጥ ባለበት የገንዘብ መጠን ልክ በግል ተጠያቂ ይሆናል።

10. ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

10.5. ሀብትን ስለመያዝ

- ባለሥልጣኑ ታክሱን በመክፈያ ጊዜው ላልከፈለ ታክስ ከፋይ የሚፈለግበትን ታክስ ማስጠንቀቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ካልከፈለ የታክስ ከፋዩ ሀብት እንዲያዝ ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑን የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ለታክስ ከፋዩ ሊሰጠው ይችላል፡፡
- ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ የሚከፍል ለመሆኑ ስጋት መኖሩን ካረጋገጠ የመያዣ ትዕዛዙን ወዲያውኑ ሊሰጥ ይችላል፡፡
- በተሰጠው ማስጠንቀቂያ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ታክሱን ካልከፈለ ወይም ስጋት መኖሩ ሲረጋገጥ ባለሥልጣኑ የመያዣ ትዕዛዙን ለታክስ ከፋዩ ሊሰጥ ወይም የታክስ ከፋዩን ሀብት በይዞታው ሥር ባደረገ በማንኛውም ሰው ላይ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡
- የመያዣ ትዕዛዙ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በስተቀር በማንኛውም የታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል፡፡
  - በሀብቱ ላይ የቀደምትነት መብት ባላቸው የገንዘብ ጠያቂዎች በተያዘ ንብረት፣
  - በማናቸውም የፍርድ ሂደት ዕገዳ በተደረገበት ወይም የአፈፃፀም ትእዛዝ በተሰጠበት ንብረት፣
  - በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ሊታገድ በማይችል ንብረት፣

10. ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

10.5. ሀብትን ስለመያዝ ….

- በታክስ ከፋዩ ንብረት ላይ የመያዣ ትዕዛዝ ከተሰጠ ወይም የሚሰጥ ከሆነ ባለሥልጣኑ በጽሑፍ በሚሰጥ ማስታወቂያ የሚያዘውን ሀብት በሚመለከት በማስረጃነት ሊያገለግል የሚችል ማንኛውንም ሰነድ ወይም መግለጫ የያዘ ማንኛውም ሰው ይህን ሰነድ ወይም መግለጫ ለባለሥልጣኑ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል።
- በመያዣ ትዕዛዙ መሠረት ንብረት በሚያዝበት ጊዜ የፖሊስ መኮንን በቦታው እንዲገኝ ባለሥልጣኑ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ሲሆን የተያዘውም ንብረት ደህንነቱ በሚረጋገጥበት ሁኔታ እንዲቀመጥ ማድረግ አለበት።
- ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩን ንብረት በሚይዝበት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች የያዘ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ይሰጠዋል፦
    - የተያዘውን ንብረት እና ያልተከፈለውን የታክስ መጠን፣
    - ታክስ ከፋዩ በማስታወቂያው በተገለጸው ሀብቱ ተይዞ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የሚፈለግበትን ታክስ የማይከፍል ከሆነ ሀብቱን እንደሚሸጠው፤

10. ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

10.5. ሀብትን ስለመያዝ ....

- ሀብት ተይዞ የሚቆይበት ጊዜ ማለት፡
  - ➢ ለሚበላሹ ዕቃዎች የዕቃዎቹን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ባለሥልጣኑ በቂ ነው ብሎ የሚወስነው ጊዜ፣
  - ➢ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ዕቃዎቹ ከተያዙ በኋላ ያለው የአስር የሥራ ቀናት ጊዜ ነው፡፡
- ታክስ ከፋዩ በሚሰጠው ማስታወቂያ የተመለከተውን ያልተከፈለ ታክስ ንብረቱ ተይዞ እስከ ሚቆይበት ጊዜ የመጨረሻው ቀን ድረስ ያልከፈለ እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ ሀብቱን በግልጽ ጨረታ በመሸጥ ከሽያጩ የሚገኘው ገንዘብ በቅደም ተከተል ለሚከተሉት ክፍያዎች እንዲውል ያደርጋል፣
  - ➢ በመጀመሪያ ደረጃ በባለሥልጣኑ በሚወሰነው መጠን ሀብቱን ለመያዝ፣ ለመጠበቅና ለመሸጥ የወጣውን ወጭ ለመሸፈን፣
  - ➢ በተሰጠው ማስታወቂያ የተመለከተውን ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ለመክፈል፣
  - ➢ የታክስ ከፋዩን ሌላ የታክስ ዕዳ ለመክፈል፣
  - ➢ ከሽያጩ ገንዘብ ላይ ቀሪ ገንዘብ ካለ ንብረቱ ከተሸጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 45 ቀናት ውስጥ ለታክስ ከፋዩ ይከፈለዋል፡፡

10. ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

10.5. ሀብትን ስለመያዝ ....

- ታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ስምምነቱን ከገለጸ ተራፊው ገንዘብ ወደፊት ለሚመጣ ማንኛውም የታክስ እዳ መክፈያነት እንዲውል ማድረግ ይቻላል።
- ከሀብት ሽያጭ የሚገኘው ገንዘብ ታክስ ከፋዩ ከሚፈለግበት የታክስ ዕዳ እና ሀብቱን ለመያዝ፣ ለመጠበቅ እና ለመሸጥ ከወጣው ወጭ ያነሰ በሚሆንበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በዚህ የአዋጅ ክፍል መሠረት ቀሪውን ዕዳ ለማስከፈል ይችላል።
- በባለሥልጣኑ የመያዣ ትዕዛዝ የተላለፈበትን ሀብት የያዘ ማንኛውም ሰው ይህንን ሀብት ያላስረከበ ወይም ለማስረከብ ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ ወጪውን ጨምሮ ካላስረከበው ሀብት ዋጋ ሳያልፍ ከታክስ ከፋዩ ለሚፈለገው ታክስ መጠን በግል ተጠያቂ ይሆናል።
- የመያዣ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚችለው ዋና ዳይሬክተሩ ወይም ለዚሁ ተግባር በዋና ዳይሬክተሩ ውክልና የተሰጠው የታክስ ሠራተኛ ይሆናል።
- የተያዘው ሀብት በባለሥልጣኑ የሚያዝና በባለሥልጣኑ ኃላፊነት ስር የሚቆይ ሲሆን ለምንም ዓይነት ዓላማ ተብሎ ለሌላ ለማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተላልፎ ሊሰጥ አይችልም።

10.6. በፋይናንስ ተቋማት የተቀመጠ ገንዘብ እና ንብረት ይዞ ስለማቆየት

- ተፈፃሚ የሚሆነው ባለሥልጣኑ በበቂ ምክንያት ከታክስ ከፋዩ ላይ የሚፈለገው ታክስ የሚሰበሰብ ስለመሆኑ ስጋት ሲኖረውና ታክሱ በአስቸኳይ መሰብሰብ ያለበት ሲሆን ይሆናል፡፡
- ባለሥልጣኑ አንድ የፋይናንስ ተቋም የሚከተሉትን እንዲፈጽም አስተዳደራዊ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
    - የታክስ ከፋዩ ሂሳቦች እንዳይንቀሳቀሱ እንዲያደርግ፣
    - በፋይናንስ ተቋሙ ውስጥ ባለ በጥንቃቄ የሚያዙ ዕቃዎች ማስቀመጫ ሣጥን ውስጥ የተቀመጠ ማንኛውም የታክስ ከፋዩ ጥሬ ገንዘብ፣ ውድ እቃ፣ የከበረ ጌጣጌጥ፣ ወይም ሌላ ንብረት እንዳይንቀሳቀስ፣
    - በጥንቃቄ በሚያዙ ዕቃዎች ማስቀመጫ ሣጥን ውስጥ ስለሚገኙ ሀብቶች ተገቢውን መረጃ ወይም በሣጥኑ ውስጥ ያሉትን ሀብቶች ዝርዝር ለባለሥልጣኑ እንዲሰጥ፣

10. ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

10.6. በፋይናንስ ተቋማት የተቀመጠ ገንዘብ እና ንብረት ይዞ ስለማቆየት ....

- ባለሥልጣኑ ለፋይናንስ ተቋሙ የዕግድ ትዕዛዝ በደረሰው በ10 የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ትዕዛዙ እንዲቀጥል ለማድረግ የሚያስችል የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
- የዕግድ ትዕዛዙ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ10 የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ የፍርድ ቤት ፈቃድ ካልተገኘ ባለሥልጣኑ የሰጠው ትዕዛዝ ተፈጻሚነት ያቆማል፡፡
- አንድ የገንዘብ ተቋም ያለምንም በቂ ምክንያት የተሰጠውን ትዕዛዝ ሣይፈፅም የቀረ እንደሆነ በትዕዛዙ ለተመለከተው የገንዘብ መጠን በግሉ ኃላፊ ይሆናል፡፡

10. ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

10.7. ያልተከፈለን ታክስ ከሦስተኛ ወገኖች ስለማስከፈል

- ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ ገንዘብ ለሚከፍል ሦስተኛ ወገን በጽሑፍ በሚሰጥ ትዕዛዝ በትዕዛዙ የተመለከተውን ገንዘብ ለባለሥልጣኑ እንዲከፍል ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል
- የክፍያ ትዕዛዙ ለታክስ ከፋዩ ገንዘብ የሚከፍል ሦስተኛ ወገን ከደመወዝ ወይም በተወሰነ የጊዜ ገደብ ከሚከፈል ሌላ ተመሳሳይ ክፍያ ላይ ቀንሶ ገቢ እንዲያደርግ በሚሆንበት ጊዜ ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ የሚቀነሰው የገንዘብ መጠን ከሚከፈለው ደመወዝ ወይም ሌላ ክፍያ (ከግብር በኋላ) አንድ-ሶስተኛ መብለጥ የለበትም።
- በጋራ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ውስጥ የሚገኝን ገንዘብ በተመለከተ የክፍያ ትእዛዝ ለከፋዩ የሚሰጠው፡-
  - ሁሉም የጋራ ሂሳቡ ባለቤቶች ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ሲኖርባቸው፣ ወይም
  - የሽርክና ማህበር ሂሳብን ሳይጨምር፣ ታክስ ከፋዩ የሌሎቹ የሂሳብ ባለቤቶች ፊርማ ወይም ፈቃድ ሳያስፈልገው ከሂሳቡ ላይ ገንዘብ ማውጣት የሚችል ሲሆን ብቻ ነው።

10.7. ያልተከፈለን ታክስ ከሦስተኛ ወገኖች ስለማስከፈል ....

- በክፍያ ትዕዛዝ መሠረት ክፍያ የሚፈፅም ማናቸውም ሰው በትዕዛዙ በተመለከተው ቀን ክፍያውን መፈፀም ያለበት ሲሆን፣ ይህም ቀን ገንዘብ ከፋዩ ለታክስ ከፋዩ ገንዘቡን ሊከፍል ከሚገባበት ቀን በፊት ወይም ገንዘቡ በታክስ ከፋዩ ስም ከተያዘበት ቀን በፊት ሊሆን አይችልም።
- የክፍያ ትዕዛዙን ለመፈፀም አልቻልኩም የሚል ገንዘብ ከፋይ የክፍያ ትዕዛዙ በደረሰው በሰባት ቀናት ውስጥ ትዕዛዙን ለመፈፀም ያልቻለበትን ምክንያት ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት።
- የክፍያ ትዕዛዙን ለመፈፀም አልቻልኩም የሚል ማስታወቂያ ገንዘብ ከፋዩ ለባለሥልጣኑ የላከ እንደሆነ ባለሥልጣኑ በጽሑፍ በተዘጋጀ ማስታወቂያ፦
  - ማስታወቂያውን በመቀበል የክፍያ ትዕዛዙን ሊሰርዘው ወይም ሊያሻሽለው ወይም
  - ለገንዘብ ከፋዩ የተላከለትን ማስታወቂያ ውድቅ ሊያደርገው ይችላል።

10.7. ያልተከፈለን ታክስ ከሦስተኛ ወገኖች ስለማስከፈል ....

- ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ በሙሉ ወይም በከፊል የከፈለ ወይም ስለታክስ አከፋፈሉ በባለሥልጣኑን ዘንድ ተቀባይነት ያለው የክፍያ ስምምነት የፈፀመ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ለከፋዩ አስተላልፎት የነበረውን የክፍያ ትእዛዝ በጽሑፍ በተሰጠ ማስታወቂያ ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል።
- ባለሥልጣኑ ለከፋዩ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ወይም ማስታወቂያ ግልባጭ ለታክስ ከፋዩ መላክ አለበት።
- ባለሥልጣኑ በከፋዩ የተከፈለውን ማንኛውንም ገንዘብ ታክሱ ከፋዩ ከሚፈለግበት የታክስ ዕዳ ላይ ያቀናንሳል።
- የሚሰጠውን ማስታወቂያ ያለምንም በቂ ምክንያት ያልተቀበለ ከፋይ በማስታወቂያው ለተመለከተው የገንዘብ መጠን በግሉ ኃላፊ ይሆናል።
- በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ሊታገድ በማይችል ንብረት ላይ ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም።

10. ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

10.8. ከሀገር መውጣትን ለመከልከል የሚሰጥ ትዕዛዝ

- ድንጋጌው ተፈፃሚ የሚሆነው ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ ወይም የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም በአንድ ኩባንያ ወሳኝ ድምጽ ያለው አባል የሚከተሉትን ክፍያዎች ሳይከፍል ከሀገር ሊወጣ ይችላል የሚል በቂ ምክንያት ሲኖረው ይሆናል፡፡
  - ይህ ሰው መክፈል የሚኖርበትን ወይም ወደፊት የሚከፈል ታክስ፣ ወይም
  - ይህ ሰው ስራ አስኪያጅ የሆነበት ኩባንያ ውሳኔ በመስጠት ረገድ የዚህ ሰው ድርሻ ከፍተኛ የሆነበት ኩባንያ መክፈል የሚኖርበትን ወይም ለወደፊቱ የሚከፈል ታክስ፣
- እነዚህ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ ከሚከተሉት አንዱን ከመፈፀሙ በፊት ከኢትዮጵያ እንዳይወጣ የሚከለክል ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡
  - በታክስ ከፋዩ ወይም ታክስ ከፋዩ ውሳኔ በመስጠት ረገድ ወሳኝ ድርሻ ባለው ኩባንያ ሊከፈል የሚገባው ወይም ወደፊት የሚከፈለው ታክስ በሙሉ እስከሚከፈል፣
  - ባለሥልጣኑ በሚቀበለው አኳኋን ታክስ ከፋዩ ታክስ ለመክፈል የክፍያ ስምምነት ሲያደርግ፤

10. ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

10.8. ከሀገር መውጣትን ለመከልከል የሚሰጥ ትዕዛዝ....

- የኢሚግሬሽንና ደህንነት ባለሥልጣን ኃላፊ የክልከላ ትዕዛዙ ሲደርሰው ትዕዛዙን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ኃላፊው የሚወስዳቸው እርምጃዎች ማንኛውንም ፓስፖርት፣ መታወቂያ ወይም ሌላ ታክስ ከፋዩ ኢትዮጵያን ለቆ ለመውጣት የሚጠቀምበትን ማንኛውንም ሰነድ መያዝና ማስቀመጥን ይጨምራል፡፡
- ሌሎች የኢሚግሬሽን ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ታክስ ከፋዩ ሀገር ለቆ እንዳይወጣ በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ የተመለከተውን ታክስ ከከፈለ ወይም ታክሱን እንደሚከፍል በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያለውን የክፍያ ስምምነት ከፈፀመ ባለሥልጣኑ ለታክስ ከፋዩ ከሀገር ለመውጣት የሚያስችለው የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡
- ሕጋዊ በሆነ መልኩ በተከናወነ ማንኛውም ተግባር ምክንያት በመንግሥት ወይም በታክስ፣ በጉምሩክ፣ በኢምግሬሽን፣ በፖሊስ ወይም በሌላ ሠራተኛ ላይ ምንም ዓይነት የወንጀል ወይም የፍትሐብሄር ክስ ሊቀርብ ወይም ሊቀጥል አይችልም፡፡
- ከሀገር መውጣትን የሚከለክል ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው በዋና ዳይሬክተሩ ወይም ይህንን ትእዛዝ እንዲሰጥ ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣን በሰጠው የታክስ ኦፊሰር ብቻ ነው፡፡

10.9. የንግድ ድርጅትን ለጊዜው ስለማሸግ

- ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው አንድ ታክስ ከፋይ በተደጋጋሚ፡-
  - በግብር ሕግ መሠረት የሚፈለግበትን ሰነድ ሳይዝ ሲቀር፣ ወይም
  - ታክሱን በመክፍያ ጊዜው ሳይከፍል ሲቀር ይሆናል፡፡
- ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ ታክስ ከፋዩ ማስጠንቀቂያ በደረሰው በሰባት ቀናት ውስጥ የሚፈለግበትን ታክስ የማይከፍል ከሆነ ወይም የሚፈለግበትን ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩን የንግድ ድርጅት ለአስራ አራት (14) ቀን በጊዜያዊነት የሚያሽግ መሆኑን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡
- ታክስ ከፋዩ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ታክሱን ካልከፈለ ወይም የሚፈለግበትን ሰነድ ካልያዘ ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩ የንግድ ድርጅት ከአስራ አራት ቀን ላልበለጠ ጊዜ በከፊል ወይም በሙሉ እንዲታሸግ የሚያደርግ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
- ባለሥልጣኑ ትዕዛዙን ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ታክስ ከፋዩ የንግድ ድርጅት መግባት የሚችል ሲሆን የማሸጊያ ትዕዛዙ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ የፖሊስ መኮንን በቦታው እንዲገኝ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

10. ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

10.10. የተላለፉ የታክስ ዕዳዎች

- አንድ ታክስ ከፋይ ከሚያካሂደው የንግድ ሥራ ጋር በተገናኘ ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ያለበት እንደሆነ፤ እና
- የንግዱን ሀብቶች በሙሉ ወይም በከፊል ግንኙነት ላለው ሰው ያስተላለፈ እንደሆነ፤
    - ❖ **ከንግዱ ሀብት ጋር ተያይዞ ያልተከፈለውን ዕዳ ሀብቱ የተላለፈለት ሰው የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡**
- ባለሥልጣኑ የተላለፈውን የታክስ ዕዳ በሙሉ ወይም በከፊል ከሀብት አስተላላፊው ላይ እንዳይጠይቅ አያግደውም፡፡

10. ታክስንና ሌሎች ክፍያዎችን ስለመክፈል

10.12. ማጭበርበር ወይም የታክስ ስወራ ሲፈፀም ስለሚኖር የታክስ ኃለፊነት

- የተመሰከረለት ኦዲተር፣ የተመሰከረለት ፐብሊክ የሂሳብ ባለሙያ ወይም ፐብሊክ ኦዲተር
  - ➢ ታክስ ከፋዩ ታክስን ለማሳነስ ወይም ታክሱን ለመሰወር እንዲችል የረዳ፣ ያበረታታ፣ የመከረ እንደሆነ፣
  - ➢ ታክስ ለማሳነስ ወይም የታክስ ስወራን በሚያስከትል መልኩ በማንኛውም መንገድ እያወቀ ከታክስ ከፋዩ ጋር ከተባበረ ወይም የድርጊቱ አጋር ከሆነ በታክስ ማጭበርበሩ ወይም በታክስ ስወራው ምክንያት ለሚከሰተው የታክስ መቀነስ ከታክስ ከፋዩ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ይኖርበታል።
- አንድ የተመሰከረለት ኦዲተር፣የተመሰከረለት ፐብሊክ የሂሳብ ባለሙያ ወይም ፐብሊክ ኦዲተር ተጠያቂ ሆኖ ከተገኘ ባለሥልጣኑ ይህንን ድርጊት፡-
  - ➢ ለተመሰከረላቸው የፐብሊክ ሂሳብ ባለሙያዎች ተቋም፣ ለኢትዮጵያ የሂሳብና የኦዲት ቦርድ ወይም ለዚህ ሰው ፈቃድ ለሚሰጠው አካል ሪፖርት ማድረግ ያለበት ሲሆን ቦርዱም የኦዲተሩን ፈቃድ እንዲሰርዘው ይጠይቃል፣ ወይም
  - ➢ የንግድፈቃድ የመስጠት ኃላፊነት ላለው ባለሥልጣን ሪፖርት ያደርጋል።

11. ማካካሻ፣ ተመላሽ እና ከታክስ ዕዳ ነጻ ስለመሆን

11.1. ለታክስ ክፍያዎች የሚሰጥ ማካካሻ

- ታክስ ከፋዩ በታክስ ዓመቱ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ለቀረበት ታክስ እና በቅድሚያ ለከፈለው ታክስ ሊያገኝ የሚገባው ማካካሻ ታክስ ከፋዩ በታክስ ዓመቱ ከሚፈለግበት የገቢ ግብር ዕዳ በሚበልጥበት ጊዜ፤ ባለሥልጣኑ በብልጫ የታየውን ገንዘብ በሚከተለው ቅደም ተከተል ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
    - ➢ በመጀመሪያ ታክስ ከፋዩ በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት የሚፈለግበትን ማንኛውንም ታክስ ለመክፈል ይውላል፤
    - ➢ ቀሪው ታክስ ከፋዩ በሌላ በማንኛውም የታክስ ሕግ የሚፈለግበትን ታክስ ለመክፈል ይውላል፡፡
    - ➢ ከዚህ ሁሉ ተራፊ ገንዘብ ካለም ታክስ ከፋዩ በጽሑፍ የተመላሽ ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 90 ቀናት ውስጥ ለታክስ ከፋዩ ይመለስለታል፡፡
- ታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ስምምነቱን ከገለጸ የተመለከተው ገንዘብ ወደፊት ለሚመጣ ማንኛውም የታክስ እዳ መክፈያነት ሊሸጋገር ይችላል፡፡
- ባለሥልጣኑ ተራፊውን ገንዘብ ለታክስ ከፋዩ ካልከፈለ፤ ዘጠናው ቀን ካለቀ ጀምሮ ተራፊው ገንዘብ እስከሚመለስበት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ወለድ የማግኘት መብት አለው፡፡

11. ማካካሻ፣ ተመላሽ እና ከታክስ ዕዳ ነጻ ስለመሆን

11.2. ሊከፈል ከሚገባው በላይ የተከፈለን ታክስ ስለመመለስ

- አንድ ግብር ከፋይ ሊከፍል ከሚገባው ታክስ በላይ የከፈለ እንደሆነ ታክሱ ከተከፈለበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ሊከፍል ከሚገባው በላይ የከፈለው ታክስ እንዲመለስለት ለባለሥልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡
- ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው ታክስ ከፋዩ ሊከፍል ከሚገባው ታክስ በላይ የከፈለውን ታክስ በሚመለከት ባለሥልጣኑ የታክስ ስሌት ማሻሻያ እንዲያደርግ የሚያስገድደው ሁኔታ የሌለ እንደሆነ ነው፡፡
- ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ በታክስ ሕግ መሠረት ሊከፍል ከሚገባው በላይ የከፈለ መሆኑን ሲያምንበት በብልጫ የተከፈለውን የገንዘብ መጠን በሚከተለው ቅደም ተከተል ሥራ ላይ ያውላል፡-
    - በመጀመሪያ (ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚቀረውን ታክስ ሳይጨምር) ታክስ ከፋዩ በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት የሚፈለግበትን ማንኛውንም ታክስ ለመክፈል ይውላል፤
    - ቀሪው ታክስ ከፋዩ በሌላ በማንኛውም የታክስ ሕግ የሚፈለግበትን ታክስ ለመክፈል ይውላል፡፡
    - ተራፊ ገንዘብ ካለ ታክስ ከፋዩ የተመላሽ ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 45 ቀናት ወስጥ ለታክስ ከፋዩ ይመለስለታል፡፡

11.2. ሊከፈል ከሚገባው በላይ የተከፈለን ታክስ ስለመመለስ....

- ታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ስምምነቱን ከገለጸ ተራፊውን ገንዘብ በማንኛውም የታክስ ሕግ መሠረት ወደፊት ለሚመጣ ማንኛውም የታክስ እዳ መክፈያነት ሊሸጋገር ይችላል።
- ባለሥልጣኑ ታክስ በስህተት ተመላሽ ያደረገ እንደሆነ ታክስ ከፋዩ በባለሥልጣኑ ሲጠየቅ በመጠየቂያ ሰነድ በተጠቀሰው ቀን በስህተት የተመለሰለትን ገንዘብ ለባለሥልጣኑ መልሶ መክፈል አለበት።
- ተመላሽ በሚጠይቀው ታክስ ከፋይ አሳሳችነት ገንዘብ በስህተት የተመለሰ እንደሆነ ታክስ ከፋዩ ገንዘቡ በስህተት በተመለሰበትና በስህተት የተመለሰው ገንዘብ ተመልሶ ለባለሥልጣኑ በተከፈለበት ቀን መካከል ላለው ጊዜ ወለድ የመክፈል ኃላፊነት አለበት።
- ታክስ ከፋዩ በአሳሳችነቱ ምክንያት እንዲከፍለው የሚገደደው ተመላሽ ታክስ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል ታክስ ከፋዩ እንደሚከፍለው ማንኛውም ታክስ ተደርጎ ይወሰዳል።

11.3. ከባድ ችግር ሲያጋጥም ስለሚሰጥ የታክስ ምህረት

- ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው ሚኒስትሩ፡-
  - ባልተጠበቀ የተፈጥሮ አደጋ ወይም ጥፋት ምክንያት ወይም ከታክስ ከፋዩ ቸልተኝነት ወይም ማንኛውም ጥፋት ጋር ባልተገናኘ ሁኔታ የተፈጠረ ከባድ የግል ችግር ምክንያት ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ በሙሉ እንዲከፍል ማድረግ የማይቋቋመው ከባድ ችግር የሚያስከትልበት መሆኑን፣ ወይም
  - በታክስ ከፋዩ ሞት ምክንያት ታክስ ከፋዩ መክፈል የሚኖርበትን ታክስ በሙሉ እንዲከፈል ማድረግ በታክስ ከፋዩ ጥገኞች ላይ ከባድ ችግር የሚፈጥር መሆኑን ሲያምንበት ነው፡፡
- ይህ ተፈጻሚ ከሆነ ሚኒስትሩ ታክስ ከፋዩ ወይም የሟቹን ታክስ ከፋይ ንብረት የሚያጣራው ውርስ አጣሪ መክፈል የሚኖርበትን ታክስና ከዚህ ታክስ ጋር በተገናኘ ለዘገየ ክፍያ የሚጠየቀውን ወለድ በሙሉ ወይም በከፊል እንዳይከፈል ሊፈቅድ ይችላል፡፡
- የዚህ አይነት የታክስ ዕዳ ምህረት ሊደረግ የሚችለው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባወጣው ደንብ ድንጋጌ መሰረት የሚሰተው የታክስ እና የዘገየ ክፍያ ወለድ ምህረት የገንዘብ መጠን ጣሪያ አስር ሚሊየን (10ሚሊዮን) ብር ይሆናል፡፡

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.1. የታክስ እና ይግባኝ የሚቀርብባቸው ውሳኔዎች የመጨረሻ ስለመሆናቸው

- ወሳኝ እና የመጨረሻ ውሳኔዎች በመሆናቸው በማናቸውም ሁኔታ በኮሚሽኑ ወይም በፍርድ ቤት ወይም በሌላ የዳኝነት ሥነ ሥርዓት ተቃውሞ ሊቀርብባቸው አይችልም።
- በታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ውሳኔው የተመለከተው የታክስ መጠን እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ትክክለኛ ስለመሆናቸው ወሳኝ ማስረጃ ነው።
- ታክስ ከፋዩ ራሱ ያሳወቀበትን ዋናውን የራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም በባለሥልጣኑ እንደ ራስ ታክስ ስሌት ማስታወቂያው ዋናው ቅጂ የተረጋገጠ ሰነድ ማቅረብ ስለማስታወቂያው ይዘት ወሳኝ ማስረጃ ነው።

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.2. በታክስ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ የቅሬታ ማስታወቂያ

- በታክስ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ የውሳኔው ማስታወቂያ በደረሰው በ21 ቀናት ውስጥ በውሳኔው ላይ የቅሬታ ማስታወቂያ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
- ቅሬታ የቀረበበት የታክስ ውሳኔ በተሻሻለ የታክስ ስሌት ላይ ከሆነ የታክስ ከፋዩ የተሻሻለውን የታክስ ስሌት የመቃወም መብት የመጀመሪያውን የታክስ ስሌት በመለወጥ፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር በተደረገው ማሻሻያ ላይ ብቻ የተገደበ ይሆናል፡፡
- በታክስ ከፋይ የቀረበ የቅሬታ ማስታወቂያ በአግባቡ እንደቀረበ የሚቆጠረው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው፡-
  - የሚቃወምበትን ምክንያቶች፣ ውሳኔውን ለማስተካከል ሊደረጉ ይገባል ብሎ የሚያምንባቸውን ማሻሻያዎች እና እነዚህን ማሻሻያዎች ማድረግ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያቶች በትክክል አሟልቶ ከያዘ፣
  - ቅሬታው ከታክስ ስሌት ጋር የተገናኘ ከሆነ ታክስ ከፋዩ መክፈል ያለበትን እና በቅሬታ ማስታወቂያው ተቃውሞ ያላቀረበበትን ታክስ የከፈለ እንደሆነ ነው፡፡
  - በታክስ ውሳኔው ላይ ቅሬታ ቢኖረውም ታክሱን ከፍሎ የቅሬታ ማስታወቂያ ማቅረብን የመረጠ ከሆነ የተወሰነበትን ታክስ ከከፈለ ነው፡፡

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.3. በቅሬታ ላይ ውሳኔ ስለመስጠት

- የቀረቡ ቅሬታዎች በነጻነት በመመርመር የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ ቋሚ የሥራ ክፍል ያቋቁማል።
- ቅሬታዎች የሚታዩበትን ሥነ-ሥርዓት፣ የሚቀርቡ የውሳኔ ሃሣቦች የሚመሠረቱባቸውን ጉዳዮች እና የውሳኔ አሰጣጡን ሥርዓት የያዘ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።
- በታክስ ስሌት ላይ የቀረበውን ቅሬታ ሲመረመር በታክስ ስሌቱ የተመለከተው የታክስ መጠን ሊጨምር ይገባል የሚል እምነት ሲኖር፣ የታክስ ስሌቱ ለሚመለከተው የታክስ ሠራተኛ ተመልሶ እንደገና እንዲታይ የውሳኔ ሃሳብ ለባለሥልጣኑ መቅረብ ይኖርበታል።
- የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ከተመረመረ በኋላ፣ ቅሬታው በሙሉ ወይም በከፊል በመቀበል ወይም ውድቅ በማድረግ ውሳኔ የሚሰጥ ሲሆን ውሳኔውም በቅሬታ ላይ የተሰጠ ውሳኔ" ተብሎ ይጠቀሳል።
- በቅሬታ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ እንዲያውቀው ያደርጋል።
- ታክስ ከፋዩ ቅሬታ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 180 ቀናት ውስጥ በቅሬታው ላይ ውሳኔ ካልሰጠ ታክስ ከፋዩ ይግባኙን ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ማቅረብ ይችላል።

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.4. ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ይግባኝ ስለማቅረብ

- ይግባኝ ሊቀርብበት በሚችል ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ ውሳኔ ማስታወቂያው በደረሰው 30 ቀናት ውስጥ የፀደቀውን ቅጽ በመጠቀም በውሳኔው ላይ የይግባኝ ማስታወቂያውን ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ሊያቀርብ ይችላል።
- በታክስ ስሌት ላይ ከቀረበ ቅሬታ ጋር በተገናኘ በታክስ ከፋይ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የሚቀርብ የይግባኝ ማስታወቂያ በአግባቡ ቀርቧል ሊባል የሚችለው፡- በክርክር ላይ ያለ ታክስ 50% (ሃምሳ በመቶ) የተከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው።
- በክርክር ላይ ያለ ታክስ ከታክሱ ጋር በተገናኘ ሊከፈል የሚገባውን ቅጣትና የዘገየ ክፍያ ወለድን አይጨምርም።
- የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የይግባኝ ማስታወቂያ የሚቀርብበት ጊዜ እንዲራዘም ስለሚቀርብ ማመልከቻ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.5. ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ይግባኝ ስለማቅረብ

- ኮሚሽኑ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው የኮሚሽኑ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማስታወቂያውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።
- የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘምለት በጽሑፍ ማመልከቻ ለሚጠይቅ ሰው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጊዜውን ሊያራዝመው ይችላል።
- በታክስ ከፋይ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ የይግባኝ ማስታወቂያ በአግባቡ ቀርቧል ሊባል የሚችለው በክርክር ላይ ያለ ታክስ 75% የተከፈለ እንደሆነ ብቻ ነው።
- ለፍርድ ቤቱ ይግባኝ የሚቀርበው በሕግ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሲሆን የይግባኝ ማስታወቂያውም በቀረበው ይግባኝ የሚነሱትን የሕግ ጉዳዮች መግለጽ አለበት።
- የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን በመስማት፣ የኮሚሽኑን ውሳኔ ሊያፀናው፣ በመሻር፣ ውሳኔን የሚተካ ሌላ ውሳኔ ሊሰጥ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለኮሚሽኑ ወይም ለባለሥልጣኑ መልሶ ሊልከው፣ ይግባኙን ወድቅ ሊያደርገው እና ተገቢ መስሎ የታየውን ሌላ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.6. ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለሚቀርብ ይግባኝ

- የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው የፍርድ ቤቱ የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማስታወቂያውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።
- የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘምለት በጽሑፍ ማመልከቻ ለጠየቀ ሰው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጊዜውን ሊያራዝመው ይችላል።

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.7. የማስረዳት ኃላፊነት እና አዲስ ማስረጃ ማቅረብ፤

- ከታክስ ውሳኔ ጋር በተገናኘ በሚደረግ ማንኛውም የታክስ ክርክር ሂደት የታክስ ውሳኔ ትክክል አለመሆኑን የማስረዳት ኃላፊነት የታክስ ከፋዩ ነው፡፡
- ይግባኝ ወይም የውሳኔ ማስተካከያ ጥያቄን የሚያቀርብ ታክስ ከፋይ በታክስ ውሳኔ ወቅት ካቀረበው የተለየ አዲስ ማስረጃን ማቅረብ አይችልም፡፡
- አዲስ ማስረጃ በቅሬታ፣ ይግባኝ ወይም ስህተትን ለማረም በሚቀርብበት ወቅት ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው፦

  ሀ/ የማስረጃው አለመታየት በታክስ ከፋዩ የታክስ እዳ ላይ ከፍተኛ ጫናን የሚያስከትል ከሆነ፤

  ለ/ ታክስ ከፋዩ ማስረጃውን ያገኘው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው በኋላ ከሆነ፤ ወይም

  ሐ/ ሰነዱ ያልቀረበው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ፤ ይሆናል፡፡

12.7. የማስረዳት ኃላፊነት እና አዲስ ማስረጃ ማቅረብ.........

"አዲስ ማስረጃ" ማለት የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው በኋላ በታክስ ከፋዩ የሚቀርብ አዲስ ሰነድ፤ መረጃ፤ ማስረጃ፤ ፍሬ-ነገር ሲሆን፤

ሀ) በመጀመሪያው የታክስ አወሳሰን ሂደት ለታክስ ባለስልጣኑ ያልቀረበ፤

ለ) ለታክስ ውሳኔ ማስታወቂያው ትክክለኛነት አግባብነት ያለው እና መሰረታዊ የሆነ፤ እና

ሐ) በተወሰነው የታክስ መጠን ወይም በታክስ ከፋዩ ግዴታ ላይ መሰረታዊ ለውጥ የሚያስከትል ነው።

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.8. የታክሱ ባለስልጣን የታክስ አለመግባባትን በመስማማት ለመፍታት ያለው ስልጣን

- የታክሱ ባልስልጣን የታክስ አለመግባባቶችን በመስማማት የመፍታት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡
- ማናቸውም በስምምነት የሚፈታ የታክስ ያለመግባባት በጽሁፍ የሚደረግ እና የተስማሚ ወገኖች ፊርማ ያረፈበት ሊሆን ይገባል፡፡
- ከላይ የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲኖሩ ጉዳዩ በማስማማት ሊታይ አይችልም፡-

  ሀ) የታክስ ማጭበርበር ወይም ሆን ተብሎ የተደረገ ታክስን የመሰወር ድርጊት መኖሩ ሲጠረጠር፤

  ለ) በማስማማት የሚደረግ ስምምነት ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት እና ከሚመለከታቸው የታክስ ሕጎች ጋር የሚጋጭ ሲሆን፤

  ሐ) ከሁለቱ ወገኖች አንዱ በሽምግልና ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ካልሆነ፡፡

- የታክሱ ባለስልጣን የመስማማት ሂደት የሚመራበትን ሥርዓት የሚወስን ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ያወጣል፡፡

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.9. የታክስ አለመግባባትን ለመስማማት ስለመምራት

- የታክስ አለመግባባት ለመስማማት ሊመራ የሚችለው በታክሱ ባለስልጣን እና በታክስ ከፋዩ መካከል የታክስ አለመግባባቱን በመስማማት ለመፍታት ስምምነት ሲደረስ ነው።
- የታክስ አለመግባባት በመስማማት እንዲፈታ የሚደረገው በአዋጁ መሰረት ቅሬታ ከቀረበ በኋላ ይግባኝ ሊቀርብበት በሚችል ውሳኔ ላይ ብቻ ነው።
- ይግባኝ ያቀረበ ማንኛውም ታክስ ከፋይ፣ ይግባኙን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ፣ ክርክሩ በመስማማት እንዲፈታ በተወሰነው ቅጽ መሰረት የጽሑፍ ጥያቄ ለታክስ ባለስልጣኑ ማቅረብ ይችላል፤
- የታክስ እርግጠኝነትንና ቀልጣፋ አሰራርን የሚያረጋግጥ ሆኖ ሲገኝ፣ ባለሥልጣኑ በታክስ ከፋዩ ስምምነት በማንኛውም የይግባኝ ክርክር ሂደት ላይ ጉዳዩን ወደ መስማማት ሊመራው ይችላል።
- የታክስ አለመግባባት ወደ መስማማት እንዲመራ መደረጉ ለአቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት ከሚቀርብ ማመልከቻ በስተቀር ሌሎች በዚህ አዋጅ የተመለከቱ የታክስ አለመግባባት መፍቻ ዘዴዎችን መጠቀምን የሚከለክል አይሆንም።

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.10. የታክስ ያለመግባባት በመስማማት እንዲፈታ ስለሚቀርብ ጥያቄ

- የታክስ አለመግባባት በመስማማት እንዲፈታ የሚፈልግ ታክስ ከፋይ ይህንኑ በመግለጽ ለታክስ ባለስልጣኑ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል።
- የታክሱ ባለስልጣን የታክስ አለመግባባቱ በመስማማት ሊፈታ የሚችል መሆን ያለመሆኑን ይወስናል።
- በዚህ መሠረት የስምምነት ጥያቄ ማቅረብ፣ ግብር ከፋዩ በባለሥልጣኑ የተወሰነውን እና አከራካሪ ያልሆነውን የታክስ መጠን የመክፈል ግዴታን አያስቀርም።

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.11. የሌሎች ሂደቶች መታገድ

- የታክስ አለመግባባቱ በመስማማት በሚታይበት ጊዜ በአዋጁ
  - ✓ አንቀጽ 88 ንዑስ አንቀጽ 1 (ይግባኝ በሚባልበት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የፈለገሰው የውሳኔው ማስታወቂያ በደረሰው በሠላሳ ቀናት ውስጥ የጸደቀውን ቅጽ በመጠቀም በውሳኔው ላይ የይግባኝ ማመልከቻ ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይችላል፡፡) እና
  - ✓ አንቀጽ 91 ንዑስ አንቀጽ 2 (ኮሚሽኑ የይግባኝ ማመልከቻ ከቀረበለት ቀን ቀጥለው ባሉት አንድ መቶ ሃያ ቀናት ውስጥ በቀረበው ይግባኝ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡) በማለት የተቀመጡት የጊዜ ገደቦች ተፈጻሚነት ታግዶ ይቆያል፡፡
- የማስማማቱ ተሳታፊ ወገኖች የታክስ አለመግባባቱን በመስማማት ለመፍታት ካልቻሉ የማስማማቱ ሂደት ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ በአዋጁ የተቀመጡት የጊዜ ገደቦች ተፈጻሚነት ይቀጥላል፡፡

12.12. አስማሚ ስለመመደብ

- የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ነፃ እና ገለልተኛ የሆነ አስማሚ ይመደባል፡፡
- የሚመደበው አስማሚ ገለልተኛ እና የሙያ ብቃት ያለው መሆን አለበት፡፡

12.13. የአስማሚው ሚና

- አስማሚው፣ ተከራካሪ ወገኖች ለክርክሩ ፍትሐዊ መፍትሄ እንዲያገኙ ለመርዳት ገለልተኛ እና አድልዎ የማያደርግ ባለሙያ ሆኖ ይሠራል፡፡
- ሂደቱን በሚመራበት ጊዜ አስማሚው የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል፦

ሀ/ ተከራካሪ ወገኖች አከራካሪ በሆኑ ነጥቦች ላይ የጽሑፍ መግለጫዎችን እና ደጋፊ ማስረጃዎችን እንዲያቀርቡ መጠየቅ፤

ለ/ የታክስ ያለመግባባት በስምምነት እንዲፈታ ለማድረግ የታክስ ባለሥልጣኑና ታክስ ከፋዩ ላለመግባባቱ መነሻ የሆኑትን የፍሬ ነገር፤ የህግ፣ የቴክኒክና የማስረጃ ጭብጦችን በሚገባ እንዲመረመሩ እገዛ ማድረግ፤

ሐ/ በማንኛውም የማስማማት ሂደቱ ደረጃ ላይ፣ ወገኖች እንዲመክሩበት የዕርቅ ስምምነት ነጥቦችን የያዘ ምክረ ሀሳብ ማርቀቅ እና ማቅረብ፣

መ/ ተከራካሪ ወገኖች ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ጉዳዩ ወደ ይግባኝ ሰሚ ወይም ወደ ፍርድ ቤት ቢቀጥል ሊኖረው የሚችለውን ውጤት በተመለከተ አስገዳጅ ያልሆነ የሙያዊ አስተያየት መስጠት፡፡

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.14. የመስማማት አካሄድ

- የመስማማት ሂደት የሚመራው በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፦

    ሀ) የማስማማቱ ሂደት ገለልተኝነትን እና ሚስጥራዊነትን መሰረት ባደረገ አኳኋን መካሄድ አለበት፤

    ለ) የአስማሚው የስራ ድርሻ የማስማማት ሂደቱን የማመቻቸት እና የውሳኔ ሐሳብ የማቅረብ እንጂ ውሳኔ መስጠት አይሆንም፤

    ሐ) የማስማማቱ ሂደት መደበኛ የሆኑ የስነ ስርአት ደንቦችን ላይከተል ይችላል።

- የታክስ አለመግባባትን በመስማማት ለመፍታት ስምምነት ከተደረሰበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ መጠናቀቅ አለበት።
- ከላይ የተደነገገው ቢኖርም የስምምነት ሂደቱ ከ60 ቀናት በላይ ሊራዘምበት የሚችልበት ሁኔታ የታክስ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.15. ሚስጥራዊነት

- ማናቸውም በማስማማቱ ሂደት የሚደረግ ግንኙነት በሚስጥር መጠበቅ አለበት።
- በህግ መሰረት ወይም በተሳታፊ ወገኖች ስምምነት ካልሆነ በስተቀር የማስማማቱ ውጤት በማናቸውም የይግባኝ መድረክ በማስረጃነት ሊያገለግል አይችልም።

12.16. ስምምነት

- ተሳታፊ ወገኖች በማስማማቱ ውጤት ከተስማሙ፤ ስምምነቱ፦

    ሀ) በጽሑፍ መደረግ ያለበት ሲሆን፤ ተሳታፊ ወገኖች ሊፈርሙበት ይገባል፤

    ለ) አስገዳጅ እና ተፈጻሚነት ያለው ይሆናል፡፡

- የታክሱ ባለስልጣን የመስማማት ስምምነቱን ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚደረስ ማንኛውም ስምምነት፣ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ታክስ ከፋይ እና የግብር ዘመን (ዘመናት) ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
- በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደረግ የፍሬ-ነገር ወይም የሕግ ክርክሩ ተመሳሳይ ቢሆንም እንኳ፣ በሌላ በማንኛውም ክርክር ወይም የግብር ዘመን ላይ በባለሥልጣኑ ወይም በሌላ ታክስ ከፋይ ላይ አስገዳጅነት አይኖረውም፡፡

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.17 ያለመስማማት

- የማስማማቱ ተሳታፊ ወገኖች በማስማማቱ ውጤት ካልተስማሙ ታክስ ከፋዩ በአዋጁ አንቀጽ 105 መሰረት ይግባኙን ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም አግባብነት ላለው ፍርድ ቤት ለማቅረብ ይችላል።

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.18 ወጪዎች

- እያንዳንዱ የማስማማቱ ተሳታፊ ለማስማማቱ የሚያስፈልገውን የራሱን ወጪ መሸፈን አለበት፡፡
- ለአስማሚው የሚከፈለው የአገልግሎት ዋጋ በታክስ ከፋዩ ይሸፈናል፡፡

12. ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠር አለመግባባት

12.19 የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም የፍርድ ቤትን ውሳኔ ስለመፈጸም

- ባለሥልጣኑ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ የተሻሻለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ መስጠትን ጨምሮ፣ ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት።
- የታክስ ስሌት ማሻሻያ የጊዜ ገደብ (የተሻሻለው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከተሰጠ በኋላ ባለው የአንድ አመት ጊዜ ውስጥ) የተመለከተው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔን ተግባራዊ ለማድረግ በሚከናወን የታክስ ስሌት ማሻሻያ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

13. መረጃን ስለመሰብሰብና ስለማስፈፀም

13.1. የታክስ ክሊራንስ

- ማንኛውም ታክስ ከፋይ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ ማመልከት ይችላል።
- ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ በታክስ ሕግ መሠረት የተጣለበትን ታክስ የመክፈል ግዴታ የፈፀመ መሆኑን ሲያረጋግጥ ማመልከቻውን ባቀረበ በ14 ቀናት ውስጥ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት።
- የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ማመልከቻ የሚያቀርበው ታክስ ከፋይ ለቀደመው ዓመት ወይም ለቀደሙት ዓመታት በታክስ ከፋይነት ያልተመዘገበ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ የተመዘገበ መሆኑን በመግለጽ ታክስ ከፋዩ ማመልከቻ ባቀረበ በ14 ቀናት ውስጥ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት መስጠት ይኖርበታል።
- ማንኛውም የሚኒስቴር መስሪያ ቤት፣ ማዘጋጃ ቤት፣ የመንግሥት የሥራ ክፍል፣ ወይም የፌደራል ወይም የክልል መንግሥት ቢሮ ወይም ሌላ ማንኛውም የመንግሥት አካል ታክስ ከፋይ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ካላቀረበ በስተቀር ማንኛውንም ፈቃድ መስጠት ወይም ማደስ ወይም በመንግሥት ጨረታ እንዲሳተፍ መፍቀድ አይችልም።

13. መረጃን ስለመሰብሰብና ስለማስፈፀም

13.1. የታክስ ክሊራንስ …

- የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ማመልከቻ ላቀረበ ታክስ ከፋይ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ላለመስጠት የወሰነ እንደሆነ ታክስ ከፋዩ ማመልከቻውን ባቀረበ በ14 ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ያልተቀበለበትን ምክንያት የሚገልጽ የውሳኔ ማስታወቂያ ይሰጠዋል፡፡
- ከላይ የተደነገገው ቢኖርም የታክሱ ባለስልጣን በሚከተሉት ምክንያቶች ያልተከፈለ የታክስ ዕዳ ላለበት ታክስ ከፋይ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የታክስ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይችላል፦

  ሀ) ታክስ ከፋዩ በዚህ አዋጅ መሰረት ስልጣን ለተሰጠው አካል የታክስ መቃወሚያ አቤቱታ፤ ይግባኝ ወይም የታክስ ክርክር ያቀረበ ከሆነ፤

  ለ) የሚፈለግበትን የታክስ እዳ ለመክፈል ከታክሱ ባለስልጣን ጋር የጸና የክፍያ ስምምነት የፈጸመ ከሆነ፤

13. መረጃን ስለመሰብሰብና ስለማስፈፀም

13.1. የታክስ ክሊራንስ ...

- ለታክስ ከፋይ የሚሰጠው የታክስ የምስክር ወረቀት ለሚከተሉት ተግባርት የሚያገለግል ይሆናል፤

  ሀ) የንግድ ስራ ፈቃድ ወይም የሙያ ፈቃድ ለማደስ፣

  ለ) በጨረታ ለመሳተፍ፣

  ሐ) ለተሽከርካሪዎች ወይም የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ዓመታዊ ምዝገባና ምርመራ /ክላውዶ/ ለማድረግ፣ እና

  መ) የባንክ ብድር ለማግኘት።

- በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የታክስ የምስክር ወረቀት፡

  ሀ) የታክስ ከፋዩን ታክስ የመክፈል ግዴታ የሚያስቀር፤ የሚያግድ ወይም ግዴታውን የተወጣ ሆኖ እንዲቆጠር የሚያስችል አይሆንም፤

  ለ) የታክሱ ባለስልጣን ያልተከፈለውን ታክስ በማስከፈል ረገድ ያለውን መብት የሚያሳጣ አይሆንም፤

  ሐ) በሂደት ላይ ያለውን የታክስ አለመግባባት ወይም ክርክር ውጤት የሚያስቀር አይሆንም፤

13. መረጃን ስለመሰብሰብና ስለማስፈፀም

13.1. የታክስ ክሊራንስ ...

- በአንቀጽ 72 መሰረት የሚሰጠው የታክስ የምስክር ወረቀት ተፈጻሚ የሚሆነው ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ለሚወሰነው የጊዜ ገደብ ሲሆን፤ በመመሪያው በሚዘረዘሩ ምክንያቶች ሊሻር ይችላል።
- በአዋጁ አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ መሰረት የተሰጠ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት በአዋጁ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ 1 በተዘረዘሩ (ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ በሚከፈል ታክስ፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ወይም በኤክሳይዝ ታክስ፤ እና ለሦስተኛ ወገን በሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ መሠረት ሊከፈል በሚገባው ገንዘብ) የታክስ አይነቶች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።
- ባንኮች ለውጭ ባለሃብት ትርፋን፣ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻውን ወይም ድርጅቱን በመሸጥ ያገኘውን ገቢ ወደ ውጭ እንዲልክ ከማድረጋቸው በፊት በትርፋ ወይም በአክሲዮን ድርሻው ወይም በሽያጭ ገቢው ላይ ግብር የከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ በታክስ ባለስልጣኑ የተሰጠ የታክስ የምስክር ወረቀት እንዲያቀርብ መጠየቅ አለባቸው።

13. መረጃን ስለመሰብሰብና ስለማስፈፀም

13.2. የመመስረቻ ጽሑፍን እና የመተዳደሪያ ደንብን ስለማቅረብ

- ማንኛውም ድርጅት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ
    - የመመስረቻ ጽሑፍ፣
    - የመተዳደሪያ ደንብ፣
    - የሽርክና ማህበር ስምምነት ወይም
    - ሌላ የመመስረቻ ወይም የምዝገባ ሰነድ ቅጂ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።
- በተጠቀሱት ሰነዶች ላይ ማንኛውም ለውጥ ሲደረግ ድርጅቱ ለውጡ በተደረገ በ30 ቀናት ውስጥ ለውጡን በጽሑፍ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት።

13. መረጃን ስለመሰብሰብና ስለማስፈፀም

13.3. ኦዲተሮች (ፐብሊክ እና የተመሰከረለት ኦዲተር)

- ኦዲተሮች የደንበኞቻቸውን የኦዲት ሪፖርት ለደንበኞቻቸው ካቀረቡበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ3 ወር ጊዜ ውስጥ የኦዲት ሪፖርቶቹን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለባቸው፡፡
- ማንኛውም ኦዲተር የኦዲት ሪፖርቶቹን ለባለሥልጣኑ ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ኦዲተሩ ግደታውን ያልተወጣ መሆኑን ለኢትዮጵያ የሂሳብና ኦዲት ቦርድ ወይም ለኢትዮጵያ የተመሠከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎች ኢንሲቴትዩት በማሳወቅ ቦርዱ ወይም ኢንስቲትዩቱ የኦዲተሩን ፈቃድ እንዲሰረዝ ይጠይቃል፡፡

13.4. በኢትዮጵያ ነዋሪ ካልሆነ ሰው ጋር የሚደረግ የአገልግሎት ውልን ስለማሳወቅ

- ምንጩ ኢትዮጵያ የሆነ የአገልግሎት ውል (የቅጥር ውልን ሳይጨምር) በኢትዮጵያ ነዋሪ ካልሆነ ሰው ጋር የሚገባ ማንኛውም ሰው ውሉን ከፈረመበት ወይም መፈጸም ከጀመረበት ቀድሞ ከመጣው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 30 ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት።

13.5. መረጃ ወይም ማስረጃ ለማግኘት ማስታወቂያ ስለመስጠት

- ማንኛውንም የታክስ ሕግ ለማስተዳደር ሲባል ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋይ ቢሆንም ባይሆንም ለማንኛውም ሰው የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ፡-
  - የራሱን ወይም የሌላ ማንኛውንም ሰው የታክስ ጉዳይ የሚመለከት በማስታወቂያው የተገለፀውን መረጃ እንዲሰጠው፣
  - የራሱን ወይም የሌላ ማንኛውንም ሰው የታክስ ጉዳዮች በተመለከተ በማስታወቂያው የተገለጸውን ማስረጃ እንዲሰጠው፣
  - ከእርሱ ወይም ከሌላ ማንኛውም ሰው የታክስ ጉዳዮች ጋር የሚገናኙ በእጁ ወይም በእርሱ ቁጥጥር ሥር ያሉ በማስታወቂያው የተገለፁ ሰነዶችን እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል።
- ይህ ጥያቄ፡-
  - በኤሌክትሮኒክ መልክ የሚገኙትን ጨምሮ ማንኛውንም መረጃ መስጠትን ወይም ሰነድ ማቅረብን በተመለከተ ልዩ መብት የሚሰጥ ወይም የህዝብ ጥቅምን የሚመለከት ሌላ ሕግ እና
  - ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታን የሚጥል ውል ቢኖርም ተፈጻሚ ይሆናል።

14. የታክስ ሕጎችን አስቀድሞ መተርጎም

- የታክስ ህጎችን አስቀድሞ ትርጉም የመስጠት ስልጣን የገንዘብ ሚኒስቴር ነው።
- የሚሰጡ ትርጉሞች በባለስልጣኑና በሚኒስቴር መ/ቤቱ አስገዳጅ ሲሆኑ በታክስ ከፋዮች ላይ ግን አስገዳጅነት የላቸውም።
- የሚሰጡ ትርጉሞች በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ እና በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ ትርጉሞች በሚል በሁለት የሚከፈሉ ሲሆን የሚኒስቴሩ ውሳኔ ተደርገው አይወሰዱም።
- በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በግብር ከፋዩ ጥያቄ መሰረት የሚሰጥ ሲሆን በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ደግሞ ያለ ግብር ከፋይ ጥያቄ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚሰጥ ትርጉም ነው።
- ትርጉሞቹ ሚኒስቴሩ የአንድን ታክስ ሕግ አፈጻፀም በሚመለከት የሰጠውን አስተያየት የሚገልፁ ስለሆነ **በትርጉሙ ያልተስማማ** ግብር ከፋይ ቅሬታ ሊያቀርብ ወይም **ትርጉሙን አስመልክቶ** በህግ ሊከራከርበት ወይም ክስ ሊያቀርብ አይችልም።

14. የታክስ ሕጎችን አስቀድሞ መተርጎም

14.1. በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ስለመስጠት

- በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በሚኒስቴሩ ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ ላይ የሚገለጽ ሲሆን የሚሰጠው ትርጉም ይዘት በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ መሆኑን የሚገልጽ ርዕስና መለያ ቁጥር ይኖረዋል፡፡
- የሚሰጠው ትርጉም ተፈጻሚነት የሚጀምረው ትርጉሙ ላይ ከተመለከተው ቀን ጀምሮ ሲሆን በትርጉሙ ላይ ምንም ቀን ካልተመለከተ በሚኒስቴሩ ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

14. የታክስ ሕጎችን አስቀድሞ መተርጎም

14.2. በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉምን ስለማንሳት

- በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በሙሉ ወይም በከፊል ሚኒስቴሩ ሊያነሳ የሚችል ሲሆን የትርጉሙ ተፈጻሚነት መቋረጥ በማስታወቂያ ከተገለፀበት ቀን ወይም በሚኒስቴሩ ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ ላይ ከወጣበት ቀን ከሁለቱ በዘገየው ቀን ይጀምራል፡፡
- ትርጉሙ ከመነሳቱ በፊት ለተጀመሩ ግብይቶች ተፈጻሚነቱ ሲቀጥል ትርጉሙ ከተነሳ በኋላ ለተጀመሩ ግብይቶች ግን ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሁለት ምክንያቶች በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ተፈፃሚነት የሚያነሳ ሲሆን ምክንያቶቹም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡፡
- በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ ከሚሆን ትርጉም ጋር የሚቃረን ሕግ ከወጣ ፤
- ሚኒስቴሩ የተለየ ትርጉም ከሰጠ ወይም ነባሩ ትርጉም ከሕጉ ወይም ከተሰጠው አዲስ ትርጉም ጋር የማይጣጣም እስከሆነ ድረስ እንደተነሳ ይቆጠራል፤

14. የታክስ ሕጎችን አስቀድሞ መተርጎም

14.3. አስገዳጅ የሆኑ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ትርጉሞች

- ማንኛውም ታክስ ከፋይ በፈጸመው ወይም ሊፈጽም ባሰበው ግብይት ላይ የአንድን ታክስ ሕግ ተፈጻሚነት በተመለከተ የሚኒስቴሩ አቋም ምን እንደሆነ የሚገልጽ ትርጉም እንዲሰጠው ግብር ከፋዩ ሚኒስቴሩን በጽሑፍ ማመልከቻ የሚጠይቅ ሲሆን የሚቀርበው ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡፡
  - ከማመልከቻው ጋር ግንኙነት ያለውን ግብይት ዝርዝር ጉዳዮችና ለግብይቱ አግባብነት ያላቸውን ሁሉንም ሰነዶች ማካተት፣
  - ትርጉሙ የተጠየቀበትን ጉዳይ በግልጽ ማመልከት፣ እንዲሁም
  - አግባብነት ያለው የታክስ ሕግ ለግብይቱ ያለውን ተፈጻሚነት በተመለከተ የታክስ ከፋዩን አስተያየት ሙሉ መግለጫ ማካተት ይገኙበታል፣
- ከላይ በተገለጸው መሠረት ለቀረበ ማመልከቻ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ60 ቀናት ውስጥ ጉዳዩን የሚመለከት ትርጉም ይሰጣል፡፡

14. የታክስ ሕጎችን አስቀድሞ መተርጎም

14.4. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ለመጠየቅ የቀረበን ማመልከቻ አለመቀበል

- በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ለማግኘት ለሚኒስቴሩ የቀረበ ማመልከቻ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥያቄው ተቀባይነት ካላገኘ ታክስ ከፋዩ በጽሑፍ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡
  - ባለሥልጣኑ ወይም ሚኒስቴሩ እንደአግባብነቱ ማመልከቻ በቀረበበት ጥያቄ ላይ በሚከተሉት ሁኔታዎች ውሳኔ ከሰጠ፡-
    - ✓ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከተሰጠው
    - ✓ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በሥራ ላይ ያለ ከሆነ
    - ✓ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በሥራ ላይ ያለ ከሆነ፤

14. የታክስ ሕጎችን አስቀድሞ መተርጎም

14.4. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ለመጠየቅ የቀረበን ማመልከቻ አለመቀበል ...የቀጠለ

- የቀረበው ማመልከቻ ታክስ ከፋዩን በሚመለከት በታክስ ኦዲት ሥር ካለ ጉዳይ ጋር የተገናኘ፣ ታክስ ከፋዩ ተቃውሞ ካቀረበበት ጉዳይ ጋር የተገናኘ ወይም ታክስ ከፋዩ ራሱ ያሰላውን የታክስ መጠን ለማሻሻል (የታክስ ስሌት እንዲሻሻል) ከቀረበ ማመልከቻ ጋር የተገናኘ ከሆነ፣
  - ✓ ፋይዳ የሌለው ወይም ህውከት ለመፍጠር የቀረበ ከሆነ፣
  - ✓ ግብይት ያልተካሄደ ሲሆን ወይም ግብይቱ ሊካሄድ እንደማይችል ምክንያት ካለ፣
  - ✓ ትርጉም መስጠት ከታክስ የመሸሽ ድንጋጌን ተፈጻሚነት የሚያካትት ሲሆን ነው።

14.5. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ስለመስጠት

- ሚኒስቴሩ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ትርጉም ሲሰጥ ለአመልካቹ ታክስ ከፋይ በጽሁፍ ማሳወቅ ያለበት ሲሆን በዚህ አይነት የሚሰጥ ትርጉም አስቀድሞ ካልተነሳ በስተቀር በትርጉሙ ለተጠቀሰው ጊዜ የሚያገለግል ይሆናል፡፡
- ወደፊት ሊከሰት የሚችልን ነገር ወይም ሌላ አግባብነት ያለውን ጉዳት ታሳቢ በማድረግ ሚኒስቴሩ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል፤
- የተሰጠው ትርጉም በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን እና ትርጉሙ የተሰጠበትን ጥያቄ መግለጽ ያለበት ሆኖ የሚከተሉትን ጉዳዮችም መያዝ ይኖርበታል፡-
    - ታክስ ከፋዩን፤
    - ለትርጉሙ አግባብነት ያለውን የታክስ ሕግ፣
    - ትርጉሙ ተፈጻሚ የሚሆንበትን የታክስ ዘመን፤
    - ትርጉሙ የሚመለከተውን ግብይት፤
    - ትርጉሙ የተመሠረተባቸውን ታሳቢዎች፣

14. የታክስ ሕጎችን አስቀድሞ መተርጎም

14.6. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉምን ስለማንሳት

- በሚኒስቴሩ በቂ ምክንያት ሲኖር በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በሙሉ ወይም በከፊል ሊነሳ ይችላል፤
- የተሰጠው ትርጉም ተፈጻሚነት እንዲነሳ የሚደረጉ ምክንያቶች
  - ከተሰጠው ትርጉም ጋር የሚቃረን ሕግ ከወጣ፤
  - ሚኒስቴሩ ከተሰጠው ትርጉም ጋር ተመሳሳይ በሁሉም ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን አዲስ ትርጉም ሲሰጥ ነዉ፤
- ከመነሳቱ በፊት ለተጀመሩ ግብይቶች የትርጉሙ ተፈጻሚ መሆኑ የሚቀጥል ሲሆን ከተነሳ በኋላ ለተጀመረ ግብይት ትርጉሙ ተፈጻሚነቱ ይቆራረጣል።

14.7. በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም መሰጠቱን ስለማሳወቅ

- ሚኒስቴሩ ግብር ከፋዩ እንዲያውቀው የሚያደርገው በኦፊሴላዊ ድረ-ገጹ ላይ በማውጣት ሲሆን ትርጉሙ የሚመለከተውን ታክስ ከፋይ ማንነት እና በትርጉሙ የተጠቀሰውን ማንኛውንም ሚስጥራዊ የንግድ መረጃ ይፋ አይደረግም፡፡
- ማንኛውም ግብር ከፋይ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ይፋ በሆነ በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም ሊጠቀም የሚችል ሲሆን ሚኒስቴሩ እና ባለሥልጣኑ በትርጉሙ ለተመለከቱት ፍሬ ነገሮች አግባብነት ላለው የታክስ ሕግ ተፈጻሚነት እና ትርጉሙ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ይፋ በተደረገው ትርጉም ይገደዳሉ፡፡
- በአንድ ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ትርጉም በዚህ አዋጅ መሰረት ሲነሳ ሚኒስቴሩ የትርጉሙ አስገዳጅነት ትርጉሙ እንደተነሳ በማስታወቂያ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ የሚቋረጥ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ ወዲያውኑ በኢፊሴላዊ ድረ-ገጽ ላይ ማውጣት አለበት፡፡

15. ግንኙነቶች፣ ቅጾችና ማስታወቂያዎች

15.1. የሥራ ቋንቋ

- የህጉ ማስፈጸሚያ ቋንቋ አማርኛ ሲሆን ባለሥልጣኑ ከዚህ በተለየ መንገድ የተደረገ ግንኙነት ወይም የቀረበ ሰነድ ዕውቅና ላይሰጠው ይችላል።

15. ግንኙነቶች፣ ቅጾችና ማስታወቂያዎች

15.2. ቅጾችን እና ማስታወቂያዎች

- ለታክስ ህጉ ማስፈፀሚያ የሚሞሉ ቅጾች፣ ማስታወቂያዎች፣ የታክስ ማስታወቂያዎች፣ መግለጫዎች፣ ሠንጠረዦች እና ሌሎች የሚፀድቁ ወይም የሚታተሙ ሰነዶች የሚዘጋጁ በባለስልጣኑ ነው።
- እነዚህ በባለሥልጣኑ የተዘጋጁና የፀደቁ ሰነዶች የታክስ ሕግ በሌላ አኳኋን ካልደነገገ በስተቀር በተቋሙ ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ ላይ ማውጣት አስገዳጅ አይደለም።
- ሆኖም ግን በቢሮዎች ወይም በፖስታ፣ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ፣ ወይም ባለሥልጣኑ በሚወሰነው ሌላ ዘዴ ሕዝብ እንዲያገኙቸው መደረግ አለበት።

15. ግንኙነቶች፣ ቅጾችና ማስታወቂያዎች

15.3. የፀደቀ ቅጽ

- በታክስ ከፋይ የሚቀርብ ማንኛውም የታክስ ማስታወቂያ፣ማመልከቻ፣ ማስታወቂያ፣መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ በፀደቀው ቅጽ መሠረት እንደቀረበ የሚቆጠረው፡-
  - የሰነዱ አይነት በባለስልጣኑ በፀደቀ ቅጽ መሠረት የቀረበ
  - ማንኛውንም ተያያዥ ሰነዶች ጨምሮ ቅጹ የሚጠይቀውን መረጃ የያዘ እና
  - ቅጹ በሚጠይቀው መሰረት ተፈርሞ ሲቀርብ ነው፡፡
  - በፀደቀው ቅፅ መሰረት ያልቀረበ ከሆነ ለአቅራቢ ሰነዱ ተቀባይነት እንዳላገኘ ወዲያውኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
  - ሆኖም ግን በፀደቀው ቅጽ መሠረት የሚፈለጉትን አብዛኞቹን መረጃዎች የያዘ ቅጽ   ባለሥልጣኑ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል፡፡

15. ግንኙነቶች፣ ቅጾችና ማስታወቂያዎች

15.4. ሰነዶች ለባለሥልጣኑ ስለሚቀርቡበት ሁኔታ

- ሁሉም ታክስ ከፋይ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ የሚጠበቅበትን የታክስ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ፣ ማስታወቂያ፣ መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ማቅረብ አለበት።
- ታክስ ከፋዩ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ግንኙነቶችን ለመቀበል ወይም ለማድረግ የሚያስችለው አቅም እንደሌለው ባለሥልጣኑ ካመነበት በአካል ወይም በመደበኛ ፖስታ በመጠቀም በጽሑፍ እንዲያቀርቡ የሚፈቅድላቸው ግብር ከፋዮች ሊኖሩ ይችላሉ።

15. ግንኙነቶች፣ ቅጾችና ማስታወቂያዎች

15.5. ማስታወቂያዎችን ስለመስጠት

- በታክስ ሕግ መሠረት ለአንድ ታክስ ከፋይ የወጣ፣ እንዲደርስ የሚደረግ ወይም የሚሰጥ ማስታወቂያ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰነድ ለታክስ ከፋዩ ቀጥሎ በቀረቡት በአራት መንገዶች ደረጃ በደረጃ በጽሑፍ ሊደርሰው ይገባል፡-
  - ለታክስ ከፋዩ ወይም ለታክስ እንደራሴው ወይም ለታክስ ወኪሉ በአካል በመስጠት ወይም የተላከውን ሰነድ የሚቀበል ሰው ካልተገኘ ማስታወቂያውን ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የታክስ ከፋዩ የንግድ ወይም መኖሪያ ቤት በር ላይ ወይም ሌላ አመቺ ቦታ ላይ በመለጠፍ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የታክስ ከፋዩ መደበኛ ወይም በመጨረሻ የሚታወቀው የንግድ ቦታ ወይም መኖሪያ ቤት በሪኩማንዴ ደብዳቤ በመላክ፤
  - በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለታክስ ከፋዩ በማስተላለፍ፤
  - ወጪው በታክስ ከፋዩ የሚሸፈን ሆኖ የፍርድ ቤት ማስታወቂያዎች በሚወጡበት ጋዜጣ ማስታወቂያውን በማውጣት፤
- ማንኛውም ታክስ ከፋይ ማስታወቂያው ወይም ሌላው ሰነድ እንዲደርሰው በተደረገበት መንገድ ሕጋዊነት ላይ ተቃውሞ ግብር ከፋዩ ሊያቀርብ አይችልም።

15.6. የኤሌክትሮኒክስ የታክስ ሥርዓትን ተግባራዊ ስለማድረግ

- ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ተግባራት ግብር ከፋዩ በኮምፕዩተር ሥርዓት ወይም በሌላ ተንቀሳቃሽ የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ መሣሪያ አማካኝነት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መሰረት ተግባራቱን እንዲፈፅም ሊፈቅድ ይችላል፡፡
    - ➢ ለመመዝገብ ወይም የታክስ መለያ ቁጥር ለማግኘት፣
    - ➢ የታክስ ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ ለማቅረብ፣
    - ➢ ማንኛውንም ክፍያ ወይም ተመላሽ ለባለስልጣኑ ለመፈጸም፤
    - ➢ ባለሥልጣኑ የሚያስተላልፈውን ማንኛውንም ሰነድ ለመላክ፣
    - ➢ መከናወን የሚኖርበትን ወይም እንዲከናወን የተፈቀደ ሌላ ድርጊት ወይም ነገር ለማከናወን፣
- ግብር ከፋዮች ተግባራቱን በኤሌክትሮኒክስ እንዲያከናወኑ የሚያስችል አቅም መኖሩ ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡
- ማንኛውም ታክስ ከፋይ እነዚህን ተግባራት ለማከናወን በሌላ ዘዴ እንዲጠቀም ባለሥልጣኑ ካልፈቀደለት በስተቀር በዚሁ ዘዴ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

15.6. የኤሌክትሮኒክስ የታክስ ሥርዓትን ተግባራዊ ስለማድረግ....

- ታክስ ከፋዩ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ግንኙቶችን ለመቀበል ወይም ለማድረግ የሚያስችለው አቅም እንደሌለው ባለሥልጣኑ ካመነበት ከላይ የተጠቀሰው ተፈፃሚ አይሆንም፡፡
- በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የታክስ ማስታወቂያ የሚያቀርብና ታክስ ሚከፍል ማንኛውም ታክስ ከፋይ እነዚህን ተግባራት ለማከናወን በሌላ ዘዴ እንዲጠቀም ባለሥልጣኑ ካልፈቀደለት በስተቀር በዚሁ ዘዴ መቀጠል ይኖርበታል፡፡
- የታክሱ ባለስልጣን የኤሌክትሮኒክስ የታክስ ስርአትን፣ የኤሌክትሮኒክስ ፈጣን ምላሽ ኮድ የያዘን ደረሰኝ አጠቃቀምን፣ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለሚፈጸም ግብይት እና ለማናቸውም ሌላ ግብይት የሚሰጥን ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ በሚመለከት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

15.7. ሰነድን የማቅረቢያ ወይም ታክስ የመክፈያ ጊዜ

- ሰነድን የማቅረቢያ፤ ታክስ የመክፈያ እና ሌላ ማናቸውም እርምጃ የሚወሰድበት ቀን
    - ቅዳሜ፣
    - እሁድ ወይም
    - በኢትዮጵያ የህዝብ በዓል ቀን ላይ ከዋለ ተግባሩ የሚፈፀምበት ቀን የሚቀጥለው የሥራ ቀን ይሆናል።

15.8. ማስታወቂያን ተቀባይነት የማያሳጣ ጉድለት

- በታክስ ሕግ መሠረት የተዘጋጀ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ ለታክስ ከፋዩ የተሰጠው ከሆነ፣
- የተሰጠው ማስታወቂያ በይዘቱ እና በውጤቱ ማስታወቂያው መሠረት ካደረገው የታክስ ሕግ ዓላማ እና መንፈስ ጋር የሚስማማ ወይም የተጣጣመ ከሆነ፣ እና
- የታክስ ስሌቱ የሚመለከተው፣ ይመለከተዋል ተብሎ የሚታሰበው ወይም ማስታወቂያው የሚመለከተው ታክስ ከፋይ በማስታወቂያው የተሰየመው የጋራ ዓላማን እና ግንዛቤን መሠረት አድርጎ ከሆነ ተቀባይነት የማያሳጣ ጉድለት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

15.8. ማስታወቂያን ተቀባይነት የማያሳጣ ጉድለት....

ይህ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ፡-

- የታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ማንኛውም ሌላ ሰነድ ለታክስ ከፋዩ በአግባቡ እንዲደርሰው እስከተደረገ ድረስ ለማስታወቂያው መሠረት የሆነው የታክስ ሕግ ማንኛውም ድንጋጌ አልተጠበቀም በሚል ምክንያት ማስታወቂያውን ተቀባይነት ማሳጣት፣
- የታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ማንኛውም ሌላ ሰነድ ፎርም አልተሟላም በሚል ውድቅ ማድረግ ወይም እንዳልተሰጠ መቁጠር ወይም እንዳልተሰጠ እንዲቆጠር ማድረግ፣ እና
- በታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ማንኛውም ሌላ ሰነድ ላይ በሚታይ ስህተት፣ግድፈት ወይም ጉድለት ምክንያት ተቀባይነት ማሳጣት፣አይቻልም።
- ስህተቱ ወይም ልዩነቱ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የተሰጠውን ታክስ ከፋይ የሚያሳስት እስካልሆነ ድረስ የታክስ ስሌት ማስታወቂያው በሚከተሉት ምክንያቶች ዋጋ ሊያጣ አይችልም።
  - በታክስ ስሌት ማስታወቂያው በተጠቀሰው የታክስ ከፋይ ስም፣ በተገለጸው የገቢ ወይም የገንዘብ መጠን ወይም እንዲከፈል በተጠየቀው የታክስ መጠን ስህተት ምክንያት፣
  - በተዘጋጀው የታክስ ስሌት እና ለታክስ ከፋዩ በተሰጠው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ መካከል በሚታይ ልዩነት ምክንያት።

15.9. የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያን ስለማስተካካል

- የታክሱ ባለስልጣን ለታክስ ከፋዩ የደረሰው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ስህተት ወይም ግድፈት ያለበት ሆኖ ካገኘው ስህተቱን ወይም ግድፈቱን ለማስተካከል በሚያስፈልግ መጠን የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያውን ሊለውጥ ይችላል።
- የታክስ ባለስልጣኑ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የሚስተካከልበትን አግባብ ሊኖር የሚገባውን የአሰራር ሂደት የሚመለከት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

15. ግንኙነቶች፣ ቅጾችና ማስታወቂያዎች

15.10. የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያን ለማስተካከል የሚያስችሉ ምክንያቶች

- በታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ ማስተካከያ ሊደረግ የሚችለው፦

  ሀ) የስሌት ወይም የሂሳብ ስህተት ያለ ከሆነ፤

  ለ) በግብር አወሳሰን ወቅት ያልታየ አግባብነት ያለው ማስረጃ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የቀረበ አዲስ ማስረጃ ያለ እንደሆነ፤

  ሐ) የታክስ ውሳኔው አስገዳጅ ከሆነው የታክስ ህጎች ትርጉም ጋር የማይጣጣም ከሆነ፤ ወይም

  መ) ታክስ የመክፈል ግዴታን በመወሰን ረገድ የተሳሳተ ውጤት የሚያስከትል ሌላ ስህተት ካለ ነው

15. ግንኙነቶች፣ ቅጾችና ማስታወቂያዎች

15.11. ለማስተካክል የሚያስችሉ ሁኔታዎች

- የታክሱ ባለስልጣን በታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ ማስተካከያ ሊያደርግ የሚችለው፦

ሀ) ስህተቱ መሰረታዊ ከሆነ እና ሊከፈል የሚገባውን ወይም ተመላሽ መደረግ ባለበት ታክስ መጠን ላይ ውጤት የሚኖረው ከሆነ፤

ለ) ማስተካከያው ሊረጋገጥ በሚችል መረጃ ወይም ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ከሆነ፤

ሐ) አዲስ ማስረጃ በመገኘቱ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ታክስ ከፋዩ ማስረጃውን ለማቅረብ ባለመቻሉ ካልሆነ በስተቀር ታክስ ከፋዩ ስህተት እንዲታረምለት ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ጉዳዩ በይግባኝ ከመታየቱ በፊት ነው።

15. ግንኙነቶች፣ ቅጾችና ማስታወቂያዎች

15.12. የታክስ ውሳኔ ማስታወቂ ማስተካከያ ማድረግ የሚቻልበት ጊዜ

- ስህተት የማረም ሂደት የሚጀመረው ታክስ ከፋዩ ስህተት ይታረምልኝ የሚል ማመልከቻ ሲቀርብ ወይም የታክሱ ባለስልጣን በራሱ ተነሳሽነት ስህተት መኖሩን ሲያምንበት ነው።
- በአንቀጽ 98 (ሐ) ላይ በተደነገገው መሰረት የታክሱ ባለልጣኑ በታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ ማስተካከያ ማድረግ የሚችለው በሚከተለው ጊዜ ውስጥ ይሆናል፦

  ሀ) የመጀመሪያው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአምስት (5) አመታት ውስጥ፤ ወይም

  ለ) ስህተቱ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ (1) አመት ውስጥ፤ ከሁለቱ በቀደመው ጊዜ፤

15. ግንኙነቶች፣ ቅጾችና ማስታወቂያዎች

15.13. የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ማስተካከያው የሚኖረው ውጤት

- በዚህ አዋጅ መሰረት የሚዘጋጀው የተስተካከለ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ፦

    ሀ) በተደረገው ማስተካከያ ልክ የመጀመሪያውን የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የሚተካ ይሆናል፤

    ለ) በዚህ አዋጅ መሰረት እንደተሰጠ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ይቆጠራል።

- ታክስ ከፋዩ ያቀረበው የማስተካከያ ጥያቄ ተቀባይነት ያላገኘ ከሆነ፣ በዚህ አዋጅ ቅሬታ ለማቅረብ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ የመጀመሪያው የውሳኔ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር ይሆናል።

15.14. የተስተካከለውን የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ስለማስታወቅ

- የታክሱ ባለስልጣን የተስተካከለውን የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በሚመለከት የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ መላክ አለበት፤

  ሀ) የስህተቱን አይነት፤

  ለ) የማስተካከያውን ምክንያት፤

  ሐ) በማስተካከያው ምክንያት ሊከፈል የሚገባውን ወይም ተመላሽ የሚደረገውን የታክስ መጠን፤

  መ) ታክስ ከፋዩ ውሳኔውን ለመቃወም ወይም ይግባኝ ለማቅረብ ያለውን መብት፤

15.15. በተደጋጋሚ ማስተካከያ በማድረግ ላይ የተጣለ ገደብ

- ማናቸውም የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በአንድ አይነት ስህተት ምክንያት ከአንድ ጊዜ በላይ ማስተካከያ ሊደረግበት አይችልም።

16. የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን

16.1. የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ስለማቋቋም

- የታክስ ይግባኝ በሚባልባቸው ውሳኔዎች ላይ ይግባኝ የሚሰማ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ የሚቋቋም ሲሆን
- የኮሚሽኑ ፕሬዘዳንት እና አባሎች የሚሾመት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው፡፡
- የኮሚሽኑ ፕሬዚዳንት በቀጥታ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው ፡፡

16.2. የይግባኝ ማመልከቻ ስለሚቀርብበት ሁኔታ

- ይግባኝ በሚባልበት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚፈልግ ሰው የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በሰላሳ (30) ተከታታይ ቀናት ውስጥ የጸደቀውን ቅጽ በመጠቀም በውሳኔው ላይ ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይችላል፡፡
- የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ኮሚሽኑ አጥጋቢ ምክንያት መኖሩን ሲያምን ሊያራዝም ይችላል፡፡
- ኮሚሽኑ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘም የሚቀርብ ማመልከቻ የሚስተናገድበትን ስነ-ሥርዓት የሚወስን መመሪያ በቀጣይ ያወጣል፡፡

16.3. ለኮሚሽኑ ሰነዶችን የማቅረብ ሥልጣን በተመለከተ

- ባለሥልጣኑ የይግባኝ ማስታወቂያው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ወይም ኮሚሽኑ በፈቀደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ሰነዶችን ለኮሚሽኑ ማቅረብ ያለበት ሲሆን ሚቀርቡ ሰነዶችና ሂደቱም የሚከተለውን ይሆናል፡-
  - የይግባኝ ማመልከቻ የቀረበበትን ይግባኝ የሚባልበት ውሳኔ ግልባጭ፣
  - በተጠቀሰው ይግባኝ የሚባልበት ውሳኔ ላይ ያልተጠቀሰ ለውሳኔው ምክንያት የሆነ መግለጫ፣
  - ውሳኔውን በይግባኝ ለማየት ለኮሚሽኑ አስፈላጊ የሆነ ማንኛውንም ሌላ ሰነድ፣
- ኮሚሽኑ በዚህ መሠረት የቀረበው የውሳኔ ምክንያቶች መግለጫ አጥጋቢ ሆኖ ካላገኘው በጽሑፍ ማስታወቂያ ባለሥልጣኑን ማስታወቂያውን በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የውሳኔውን ምክንያቶች የሚያብራራ ተጨማሪ መግለጫ እንዲያቀርብ ያዛል።
- ኮሚሽኑ ለይግባኙ አወሳሰን ሌሎች ሰነዶችን ማየት ጠቃሚ ነው ብሎ ሲያምን ባለሥልጣኑን በጽሑፍ ማስታወቂያ በማስታወቂያው በተገለጸው ጊዜ ውስጥ እነዚህን ሰነዶች እንዲያቀርብ ሊያዝ ይችላል።
- ባለሥልጣኑ በዚህ መሠረት ለኮሚሽኑ ያቀረበውን የማናቸውንም መግለጫ እና ሰነድ ቅጅ ለይግባኝ ባዩ ይሠጣል።

16. የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን

16.4. የኮሚሽኑ አሠራር ሥርዓት

- ፕሬዝዳንቱ ከኮሚሽኑ ችሎቶች የአንዱ አባል በመሆን መገልገል የሚችል ሲሆን በይግባኝ የተነሱትን ጭብጦች ግምት ውስጥ በማስገባት እንደአስፈላጊነቱ ይግባኙን ለመስማት አባላት ይመድባል፡፡
- የኮሚሽኑን አሰራር በተመለከተ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
- ማንኛውም የኮሚሽኑ አባል በሚያየው ማንኛውም ጉዳይ በአባልነቱ ከሚያከናውነው ተግባር ጋር ሊጋጭ የሚችል ቁሳዊ፣ የገንዘብ፣ ወይም ሌላ ጥቅም ሲኖር ይህንኑ ጥቅም ለፕሬዝዳንቱ መግለጽ አለበት፡፡ ፕሬዝዳንቱም ይህንን ጥቅም በመመዝገብ አባሉ በይግባኝ ሰሚነት እንዳይሳተፍ ማድረግ አለበት፡፡
- የኮሚሽኑ ፕሬዚዳንት የይግባኝ ማመልከቻ ስለሚቀርብበት ሁኔታ በተመለከተ የሚቀርብን ይግባኝ የክልል የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን እንዲያይ የውክልና ሥልጣን ሊሰጥ ይችላል፡፡

16. የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን

16.5. የኮሚሽኑ ውሳኔ አሰጣጥ በተመከለተ

- ኮሚሽኑ ይግባኝ ማመልከቻ ከቀረበለት ቀን ቀጥለው ባሉት 120 ቀናት ውስጥ ውሳኔ የሚሰጥ ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከ60 ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል ሆኖም ግን እነዚህን ጊዜ ገደቦች ኮሚሽኑ ሳያከብር ቢቀር የሰጠውን ውሳኔ ተቀባይነት ሊያሳጣው አይችልም።
- የቀረበው ይግባኝ የታክስ ስሌትን የሚመለከት ከሆነ ኮሚሽኑ፥ በታክስ ስሌቱ የተወሰነውን የገንዘብ መጠን ሊያፀናው፣ ሊቀንሰው፣ሊጨምረው ወይም ስሌቱን በሌላ አኳኋን ሊያሻሽለው፣ ወይም በሚሰጠው መመሪያ መሠረት እንደገና እንዲመለከተው የታክስ ስሌቱን ለባለሥልጣኑ ሊመልሰው፣ ይችላል።
- ኮሚሽኑ የውሳኔውን ግልባጭ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሰባት ቀናት ውስጥ ለእያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን የሚሰጥ ሲሆን ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ወይም ኮሚሽኑ በውሳኔ ማስታወቂያው ከተገለጸው ሌላ ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል ባለሥልጣኑም በደረሰው 30 ቀናት ጊዜ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ሁሉ መውሰድ አለበት።
- ኮሚሽኑ የሚሰጠው ውሳኔ ውሳኔው የተመሠረተባቸውን ምክንያቶች፣ መሠረታዊ በሆኑ የፍሬነገር ጉዳዮች ምርመራ የተገኘውን ውጤት እና ለውሳኔው መሠረት የሆነውን ማስረጃ ወይም ለውሳኔው መሠረት የሆነውን ሌላ ነገር በማካተት ለባለስልጣኑ ማስተላለፍ አለበት።

17. ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

17.1. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

- ማንኛውም የታክስ ወኪልነት የሚፈልግ ድርጅት ወይም ግለሰብ ለባለስልጣኑ ማመልከት አለበት፡፡
- አመልካቹ አገልግሎቱን ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ ሰው መሆኑ ሲረጋገጥ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ይሰጠዋል ወይም ባለስልጣኑ ውሳኔውን በጽሁፍ ያሳውቀዋል፡፡
- የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ማለት ታክስ ከፋዩን በመወከል የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ነው፡፡
  - ➢ የታክስ ማስታወቂያ ማዘጋጀት፤
  - ➢ የቅሬታ ማስታወቂያ ማዘጋጀት፤
  - ➢ የታክስ ሕጎችን አፈጻጸም ምክር መስጠት፤
  - ➢ ከባለሥልጣኑ ጋር ለሚኖሩ ጉዳዮች መወከል፤
  - ➢ ከባለሥልጣኑ ጋር ማንኛውንም ሌላ የሥራ ግንኙነት ማድረግ፤

17. ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

17.2. ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ የመስጠት ሂደት

- የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተ ግለሰብ ወይም የሽርክና ማህበር የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ መሆኑን በማረጋገጥ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
- የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተ ኩባንያ የኩባንያው ተቀጣሪ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እና ተስማሚ መሆኑን በማረጋገጥ የኩባንያው እያንዳንዱ ዳይሬክተር፣ ሥራ አስኪያጅ እና ሌላ ስራ አስፈጻሚ ባለሥልጣን አመልካቹ መልካም ጠባይና ሥነ-ምግባር ያለው መሆኑ በማረጋገጥ ሲቀርብ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
- የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት የሚያመልክት ሰው ብቁ እና ተስማሚ መሆኑን ለመወሰን የሚረዱ ቋሚ ሥፈርቶችን በታክስ አስተዳደር ደንብ ተደንግጓል፡፡
- ባለሥልጣኑ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የሰጣቸውን ሰዎች ዝርዝር አመቺ ሆኖ ባገኘው መንገድ በየጊዜው ይፋ ያደርጋል፡፡
- የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የሙያ ፈቃድ በመሆኑ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው የንግድ ሥራ ፈቃድ ተሰጥቶት እንደሆነ ሥራውን የሚሠራው በታክስ ወኪልነት ብቻ ነው፡፡
- የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ለሶስት አመታት የሚፀና ይሆናል፡፡

17. ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

17.3. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ስለማደስ

- የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱ እንዲታደስለት ለባለስልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡
- የፈቃዱ የአገልግሎት ጊዜ ባበቃ በ21 ቀናት ወይም ባለሥልጣኑ በሚፈቅደው ከዚህ በዘገየ ጊዜ ውስጥ እንዲታደስ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
- ፈቃዱ እንዲታደስለት ያመለከተ ሰው የታክስ ወኪልነት ለማግኘት የተመለከቱትን ቅድመሁኔታዎች አሟልቶ እስከቀጠለ ድረስ ለባለሥልጣኑ ያመለከተን ሰው ፈቃድ ያድሳል፡፡
- ለባለሥልጣኑ ፈቃዱ እንዲታደስለት ለጠየቀ አመልካች ባቀረበው ማመልከቻ ላይ ስለተሰጠው ውሳኔ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

17. ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

17.4. የታክስ ወኪልነት አገልግሎቶች ላይ ስለሚኖር ገደብ

- የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ከተሰጠው ሰው በስተቀር ማንም ሰው በክፍያ የታክስ ወኪልነት አገልግሎት መስጠት አይችልም።
- ለታክስ ወኪልነት አገልግሎት በተሰጠው ትርጉም ከተካተቱት አገልግሎቶች ውጪ በመደበኛ የሙያ አገልግሎቱ ሂደት የታክስ ወኪልነት አገልግሎት በሚሰጥ የጥብቅና ፈቃድ ያለው ሰው ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

17. ለታክስ ወኪሎች ፈቃድ ስለመስጠት

17.5. የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ስለመሰረዝ

- የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሥራውን ከማቋረጡ በፊት በ7 ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።
- የታክስ ወኪልነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው በሙያው መሥራት ካልፈለገ የታክስ ወኪልነት ፈቃዱ እንዲሰረዝለት ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማመልከት አለበት።
- ከባለሥልጣኑ የተሰጠ የታክስ ወኪልነት ፈቃድ እንዲሰረዝ የሚያደርጉ ምክንያቶች፣
    - ተዘጋጅቶ የቀረበ የታክስ ማስታወቂያ በማንኛውም መሠረታዊ ጉዳይ ሀሰት ሆኖ ሲገኝ፤
    - የሙያዊ ብቃት መስፈርትን ይዞ መቀጠል ሲቀር፤
    - ሙያዊ የሥነ-ምግባር ጉድለት መፈፀሙ ሲታመን ፤
    - የታክስ ወኪሉ የታክስ ወኪልነት ሥራውን መሥራት ሲያቆም፤
    - እንዲሁም የታክስ ወኪሉ ኩባንያ ወይም የሽርክና ማህበር ሲሆን የኩባንያው ወይም የሽርክና ማህበሩ ህልውና ሲያከትም፤
    - የፈቃድ አገልግሎት ጊዜ ሲያበቃ እና የታክስ ወኪሉ ፈቃዱ እንዲታደስለት ማመልከቻ ሳያቀርብ ሲቀር ነው፤

ክፍል ሶስት

አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣቶች

1. የመመርመር ሥልጣን

1.1. በማስታወቂያ መረጃ ወይም ማስረጃ መጠየቅ

- የታክስ ህጎችን በማስተዳደር ግብር/ታክስ ከፋይ ቢሆንም ባይሆንም ለማንኛውም ሰው ሰነዱ የሚቀርብበትን ቦታ፣ ጊዜና የሰነዱን ዓይነት የሚገልጽ የጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት ባለሥልጣኑ ማንኛውም ዓይነት መረጃ እንዲሰጠው ወይም እንዲቀርብለት መጠየቅ የሚችል ሲሆን፣
- በባለሥልጣኑ የሚጠየቀው መረጃ የኤሌክትሮኒክስ መረጃን ጨምሮ በማስታወቂያው የተጠቀሰው መረጃ ሌላ ልዩ መብት የሚያስጥ ወይም የህዝብ ጥቅምን የሚመለከት ወይም ሚስጢር የመጠበቅ ግዴታን የሚጥል ውል ወይም ስምምነት ቢኖርም መረጃው መስጠት ይኖርበታል፡፡
- ይህ ለባለሥልጣኑ የተሰጠው ሥልጣን ልዩ መብት በሚያሰጡ የህግ ድንጋጌዎች የህዝብን ጥቅም በሚመለከቱ ገደቦችና ሚስጢር የመጠበቅ ግዴታን በሚጥሉ ውሎች ወይም ስምምነቶች የማይገደብ ነው፡፡

1. የመመርመር ሥልጣን

1.2. የመግባትና የመበርበር ሥልጣን

- ማንኛውንም የታክስ ህግ ለማስተዳደር ሲባል ባለሥልጣኑ ያለማስታወቂያ በማንኛውም ጊዜ፣
- በማንኛውም ግቢ ወይም ቦታ ገብቶ ማንኛውንም ዕቃ ወይም ንብረት የመበርበርና የመያዝ/ወስዶ ለታክስ ህጉ አፈጻጸም የመጠቀም፣
- ማንኛውንም ሰነድ ወይም የመረጃ ማከማቻ ቅጂ ወይም ዋናውን የመያዝና ወስዶ ለታክስ ህጉ አፈጻጸም የመጠቀም፣
- ማንኛውንም ለታክስ አወሳሰን የሚጠቅም መረጃ የታክስ ከፋዩን የታክስ ግዴታ ለመወሰን ወይም ለማንኛውም የታክስ ክርክር እስካስፈለገበት ጊዜ ድረስ ይዞ ማቆየት ይችላል።
- የታተመ መረጃ ወይም በመረጃ ማጠራቀሚያ መሣሪያ የተከማቸ መረጃ ያልተሰጠው እንደሆነ የመረጃውን ቅጂ ለመውሰድና አስፈላጊ ለሆነ ጊዜ መሣሪያውን ይዞ ማቆየት ይችላል።

1. የመመርመር ሥልጣን

1.2. የመግባትና የመበርበር ሥልጣን ....

- በዚህ ሥልጣን መሥራት የሚችለው ዋና ዳይሬክተሩ ወይም እርሱ የወከለው ሠራተኛ ብቻ ሲሆን፣ ውክልና የተሰጠው ሠራተኛ በዚህ ሥልጣን እንዲሰራበት የተፈቀደለት መሆኑን እንዲያሳይ ሲጠየቅ ለቦታው ወይም ለግቢው ባለቤት ወይም ባለይዞታ የጽሁፍ ማስረጃ ማሳየት አለበት።
- ይህን ማስረጃ ማቅረብ ካልቻለ የተባለውን ሥራ መስራት አይችልም።
- መረጃው የሚፈለግበት ማንኛውም ሰው መረጃውን ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ ያለበት ሲሆን፡-
    - ለሚቀርብለት ጥያቄ በጽሁፍ ወይም በቃል መልስ የመስጠት ግዴታ፣
    - የመረጃ ማከማቻው የሚስጢር ቁልፍ ካለው የቁልፉን ሚስጢር ኮድ መስጠት አለበት።
    - መረጃው ወይም የመረጃ ማከማቻው የተያዘበት ሰው በራሱ ወጪ በባለሥልጣኑ የመደበኛ የሥራ ሰዓትና ባለሥልጣኑ በሚወስናቸው ቅድመ ሁኔታዎች መሠረት ቅጂውን መውሰድ ይችላል።

1. የመመርመር ሥልጣን

1.2. የመግባትና የመበርበር ሥልጣን ....

- በዚህ መሠረት ለተወሰደና ለተያዘ መረጃ በባለሥልጣኑ የተወከለው የታክስ ሠራተኛ በፊርማው ማረጋገጫ መስጠት አለበት።
- ይህ መረጃን የመውሰድና የመያዝ ሥልጣን በሌላ በማንኛውም ህግ ወይም ውል ገደብ አይደረግበትም።
- ስለሆነም የታክስ ህግን ለማስፈጸም የሚያስችል መረጃ ለያዘ ማንኛውም ሰው የመረጃውን ዓይነትና ሁኔታ እንዲሁም መረጃውን የሚያቀርብበትን ጊዜና ቦታ የሚገልጽ ማስታወቂያ በመስጠት መረጃውን ወይም ሰነዱን ለባለስልጣኑ እንዲያቀርብ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ውክልና የሰጠው የታክስ ኦፊሰር ትዕዛዝ ማስተላለፍ ይችላል።
- መረጃውን እንዲያቀርብ የተጠየቀው ወይም የታዘዘው ግለሰብ ወይም ድርጅት መረጃውን ለማቅረብ ፈቃደኛ ካልሆነ ባለስልጣኑ መረጃው ይገኝበታል ብሎ የገመተውን ማንኛውንም ቤት ወይም ቦታ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማንኛውም ጊዜ የመበርበርና የተገኘውን ጠቃሚ መረጃ ወይም ንብረት የመያዝ ሥልጣን ለባለስልጣኑ ተሰጥቷል።

1.2. የመግባትና የመበርበር ሥልጣን ....

- ከዚህም በተጨማሪ የመተባበር ግዴታውን ያልተወጣ ሰው በወንጀል የሚጠየቅ በመሆኑ ወዲያወኑ ፌዴራል ፖሊስ ግለሰቡን በቁጥጥር ሥር አውሎ የወንጀል ምርመራ እንዲደረግበት የታክስ ኦፊሰሩ ለፌዴራል ፖሊስ መጻፍና መረጃውን ማስተላለፍ ይኖርበታል። በዚህም
  - የታክስ ህጎችን አስተዳደር ማደናቀፍ ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት፣
  - የመተባበር ግዴታን አለመወጣት ግለሰቡን ወይም ድርጅት ከሆነ ኃላፊው በብር 5000 የገንዘብ መቀጫ ያስቀጣል።
- ሲጠቃለል ለባለሥልጣኑ በአዋጅ የተሰጠው፣
  - መረጃን የመጠየቅ፣
  - ሰነድን የመመርመር፣
  - ቤትና ቦታን ወይም ይዞታን የመበርበ፣
  - ሰነድን ወይም መረጃን የመያዝ ወይም ወስዶ ለታክስ አስተዳደር ዓላማ የመጠቀም ሥልጣን የህዝብና የግል ጥቅምን እንዲሁም የግል መብትን ለማስከበር በወጡ ህጎች ወይም ሚስጥራዊነትን ለማስጠበቅ በተደረጉ የውል ስምምነቶች አይታገድም።

1. የመመርመር ሥልጣን

1.3. የመመርመርና የመበርበር ሥልጣን ህገ መንግስታዊነት

የህገ መንግስቱ የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

- ማንኛውም ሰው የግል ህይወቱ፣ ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው፤ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታ ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል፡፡
- ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውና የሚጻጻፋቸው፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሚዩኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም፡፡
- የመንግስት ባለሥልጣኖች እነዚህን መብቶች የማስከበር (እና የማክበር) ግዴታ አለባቸው፡፡
- አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነትን በማረጋገጥ፣ የህዝብን ሰላም በማስጠበቅ፣ ወንጀልን በመከላከል፣ ጤናንና የህዝብን የሞራል ሁኔታ በማስጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነጻነት በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሰረቱ ዝርዝር ህጎች መሰረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም፡፡

1. የመመርመር ሥልጣን

1.3. የመመርመርና የመበርበር ሥልጣን ህገ መንግስታዊነት

የህገ መንግስቱ የንብረት መብት

- ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል። ይህ መብት የህዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል በሌላ ሁኔታ በህግ ካልተወሰነ በስተቀር ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረት የመሸጥ፣ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል።
- ንብረት ማለት አንድ ሰው በጉልበቱ (በድካሙ)፣ በመፍጠር ችሎታው ወይም በካፒታሉ ያፈራው ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት ነው።
- ለባለሥልጣኑ የተሰጠውን የመመርመርና የመበርበር ሥልጣን ከላይ ከተመለከተ ከህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ሲታይ፣
  - የግል ህይወት መከበርና መጠበቅን በተመለከተ ህገ መንግስቱ ይህ መብት ወንጀልን ለመከላከልና ብሄራዊ የኢኮኖሚ ደህንነትን ለማረጋገጥ ሲባል በሚወጣ ዝርዝር ህግ ገደብ ሊጣልበት እንደሚችል ያመለክታል።
  - መረጃም የአንድ ሰው ሃብትንና ንብረት ሊሆን ይችላል። ስለሆነም ባለመረጃው የመረጃው ባለቤት ወይም ባለይዞታ የመሆንና በመረጃው የመጠቀም ወይም መረጃውን የማስተላለፍ ህገ መንግስታዊ መብት ያለው ቢሆንም ይህ መብት በህግ ገደብ ሊጣልበት እንደሚችል በህገ መንግስቱ ተመልክቷል።
  - በኢትዮጵያ ፍጹም የሆነ ጥበቃ (absolute protection) የሚደረግለት ምንም ዓይነት መብት የለም።

1. የመመርመር ሥልጣን

1.3. የመመርመርና የመበርበር ሥልጣን ህገ መንግስታዊነት

የህገ መንግስቱ የንብረት መብት

- በህገ መንግስቱ አንቀጽ 26 እና 40 የተመለከቱት መብቶች ከማስከበር ይልቅ ወንጀልን መከላከልና ብሄራዊ የኢኮኖሚ ደህንነትን ማረጋገጥ የመንግስት ቀዳሚ አጀንዳ (Priority) በመሆኑ፡-
  - የግል መብቶች (right of privacy)፣
  - ሚስጥርን የመደበቅ መብት (right of sececy and confidentiality)፣
  - በንብረት የመጠቀም መብት (right to use of property) እና ሌሎች
  - ከውል የሚመነጩ መብቶች በሙሉ ለባለስልጣኑ የተሰጠውን መመርመርና የመበርበር ሥልጣን አያግዱም፡፡
- በመሆኑም የባለሥልጣኑ የመመርመርና የመበርበር ሰፊ ሥልጣን ህገ መንግስቱ በሚፈቅደው መሰረት በማቋቋሚያ አዋጁ አንቀጽ 6(11) እና በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 65 እና 66 ላይ በዝርዝር ህግ የተደነገገ በመሆኑ በህገ መንግስሥት ጉዳዩን አስመልክቶ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች የሚቃረን አለመሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.1. በፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ አጠቃላይ የግብር ከፋይ ግዴታዎች

ማንኛውም የታክስ ግዴታ የሚመለከተው ሰው፡

- በግብር ከፋይነት የመመዝገብ፣
- በባለሥልጣኑ የተፈቀደ ደረሰኝ የማሳተምና የመጠቀም፣ ግብይትን በደረሰኝ ብቻ የማከናወን፣
- ተገቢነት ያላቸው ሰነዶች የመያዝ፣
- ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ፣
- በህግ በተመለከተው ጊዜ ገቢውን ወይም ሽያጬን አሳውቆ ትክክለኛ ግብሩን/ታክሱን የመክፈል፣
- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ የማስቀረትና ለባለስልጣኑ ገቢ የማድረግ፣
- ህጋዊና ትክክለኛ ደረሰኖችንና ሰነዶችን ብቻ የመጠቀም፣
- ለታክስ ተገቢነት ያላቸው ሰነዶችን በህጉ ለተመለከተው ጊዜ ያህል ይዞ የመቆየት፣
- በታክስ ደረሰኝና ሌሎች የግብይት ሰነዶች ላይ የገዥውን ወይም የአገልግሎት ተቀባዩን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የመፃፍ ግዴታዎች ተጥሎበታል።

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.2. ህጋዊ ውጤቶች

2.2.1.አስተዳደራዊ ቅጣቶች

- በታክስ ከፋይነት መመዝገብ ሲገባው ያልተመዘገበ እንደሆነ መመዝገብ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ለምዝገባ እስካመለከተበት ወይም በታክስ አስተዳደሩ አነሳሽነት እስከተመዘገበበት ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ መከፈል ያለበትን ታክስ 25% መቀጮ እንዲከፍል ይደረጋል፤ ይሁንና በዚህ ጊዜ ውስጥ የሚከፈል ግብር ከሌለ ለየወሩ ብር 1,000 ቅጣት ይከፍላል፤
- ከግብር ከፋይነት እንዲሰረዝ ያልጠየቀ ለየወሩ ብር 1,000 ብር መቀጫ ይከፍላል፣
- ታክስ ከፋይ መያዝ የሚጠበቅበትን ማንኛውንም ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ ሰነድ ላልያዘበት ታክስ ዘመን የግብሩን 20% መቀጮ የሚከፍል ሲሆን፣ የሚከፈል ታክስ እንኳን ባይኖር ለገቢ ግብር በዓመት ብር20,000፣ ለሌሎች ታክሶች በየወሩ ብር2,000 ቅጣት ይከፍላል፡፡

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.2. ህጋዊ ውጤቶች

2.2.1.አስተዳደራዊ ቅጣቶች

- የታክስ ማስታወቂያ ለታክስ አስተዳደሩ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ የደረጃ “ሀ” ግብር ከፋይ ለአምስት ዓመታት፣ ክርክር ያለባቸው ከሆነ ክርክሩ እስከሚጠናቀቅ ሰነዶችን ይዞ ያለማቆየት ለደረጃ “ሀ” ታክስ ከፋይ ብር 50,000 ቅጣት ያስከፍላል፣ አዲስ ማስረጃ ያቀረበ ከሆነ በታክስ ሕጉ መሠረት ሰነዱ በታክስ አወሳሰን ወቅት አስቀድሞ ባለመቅረቡ ምክንያት ሊከፈል ይገባ የነበረውን የታክስ ዕዳ 10% ቅጣት ይከፍላል።
  - የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በደረሰኝ ላይ አለመጻፍ ቁጥሩ ባልተጻፈበት በእያንዳንዱ ደረሰኝ ብር 3,000 ያስቀጣል፣
  - የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ለሌላ ሰው የሰጠ ብር 10,000 ይቀጣል፣
  - ከሁለት ዓመት በላይ የሂሳብ ሰነድ ያለመያዝ የንግድ ፈቃድ ስረዛን ያስከትላል፣
  - የሌላ ሰው TIN የተጠቀመ ብር 10,000 ይቀጣል።
  - የግብር ማስታወቂያ ማዘግየት 5% ያስቀጣል(25% እስኪሞላ ድረስ)
  - ግብር/ታክስ ሳይከፈል ማዘግየት ለአንድ ወር 5% ከዚያ በላይ ለሆነው ጊዜ ተጨማሪ 2% መቀጫ ያስከፍላል።

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.2. ህጋዊ ውጤቶች

2.2.1.አስተዳደራዊ ቅጣቶች

- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ያልቀነሰ ወይም ቀንሶ ገቢ ያላደረገ ያልተቀነሰውን ወይም ገቢ ያልተደረገውን ግብር 10% ይቀጣል፡፡
- እንዲሁም የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ፣ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ፣ ዋና የሂሳብ ሹም ወይም ታክስ ተቀንሶ መያዝ እንዳለበትና የተያዘውም ታክስ መከፈል እንዳለበት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ሠራተኛ እያንዳንዳቸው ብር 2,000 ይቀጣሉ፡፡
- ለተጨማሪ እሴት ታክስ አለመመዝገብ በየወሩ 2,000 ብር ያስቀጣል፡፡
- ባልተመዘገበበት ጊዜ ላከናወነው ግብይት ሊከፈል የሚገባውን ታክስ 100% ይቀጣል፡፡
- ታክስን ለማሳነስ ወይም ተመላሽ እንዲጨምር ለማድረግ ትክክለኛ ያልሆነ ደረሰኝ የሰጠ ሰው ብር 50,000 ይቀጣል፡፡
- ደረሰኛ መስጠት ሲገባው ያልሰጠ ባልሰጠው በእያንዳንዱ ደረሰኝ ብር 100,000 ይቀጣል፡፡
- ታክስ አሳንሶ ማሳወቅ ለመጀመሪያ ጊዜ 10%፣ ለሁለተኛ ጊዜ 30%፣ ለሦስተኛ ጊዜ 40% መቀጮ ያስከትላል፡፡
- ታክስ ላለመክፈል የሚደረጉ ጥረቶች ያልተከፈለውን ታክስ እጥፍ መቀጫ ያስከፍላል፡፡

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.2. ህጋዊ ውጤቶች

2.2.2.የኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት አለመከተል

- ታክሱን በኤሌክትሮኒስ ሥርዓት አሳውቆ እንዲከፍል የተጠየቀ ግብር ከፋይ በዚሁ መሠረት ያልፈጸመ እንደሆነ ብር 50,000 ይቀጣል።

2.2. ህጋዊ ውጤቶች

2.2.3. በድርጅቶች የሚፈጸሙ ወንጀሎች

- የታክስ ህግን በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመው ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ በተፈጸመበት ወቅት የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ፣ የፋይናንስ ኃላፊ ወይም በተመሳሳይ የኃላፊነት ቦታ ላይ ያለ ሰው ድርጊቱ እንዲፈጸም የፈቀደ፣ ያዘዘ ወይም የተባበረ እንደሆነ ወንጀሉን እንደፈጸመ ይቆጠራል።
- ከላይ የተደነገገው ቢኖርም ስራ አስኪያጁ፣ የፋይናንስ ኃላፊው ወይም በተመሳስይ የኃላፊነት ቦታ ላይ ያለው ሰው የሚከተሉትን ያስረዳ እንደሆነ በወንጀሉ ተጠያቂ አይሆንም፦

ሀ) ወንጀሉ የተፈጸመው ከርሱ እውቅና ውጪ መሆኑን፣

ለ) የዚህ አይነቱ ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል የሚያስችል ውስጥ ቁጥጥር ስርአት የዘረጋ መሆኑን፣

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.2. ህጋዊ ውጤቶች

2.2.4.ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ

- የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ማንኛውም ግብር ከፋይ፡-
  - እውቅና ያልተሰጠውን መሣሪያ ተጠቅሞ ከተገኘ ለእያንዳንዱ መሣሪያ ብር 50,000፣
  - በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ ሌላ ደረሰኝ ከተጠቀመ ብር 50,000፣
  - በመሣሪያው ላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም የፊሲካል ማስታወሻው እንዲቀየር ያደረገ ወይም ይህን ለማድረግ ሙከራ ያደረገ ብር 100,000
  - በመሣሪያው ላይ ፍተሻ (ኦዲት) እንዳይደረግ የተከላከለ ወይም የቴክኒክ ምርመራ በየዓመቱ ያላደረገ ብር 25,000
  - ከአገልግሎት ማዕከል ጋር ውል ካልፈጸመ ወይም መሣሪያውን ከተርሚናል ጋር ሳያያይዝ ከተጠቀመ ወይም የመሣሪያው ምርመራ መዝገብ ከመሣሪያው ጎን እንዲቀመጥ ካላደረገ ወይም በተመላሽ መዝገብ ሳይመዘገብ የተመላሽ ደረሰኝ ከሰጠ ብር 25,000፣

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.2. ህጋዊ ውጤቶች

2.2.4.ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ

- መሣሪያው አገልግሎት መስጠት ሲያቋርጥ (ሲሰረቅ ወይም ሲጐዳ) በሦስት ቀናት ውስጥ ወይም ሲበላሽ በአራት ሰዓት ውስጥ ለአገልግሎት ማዕከሉና ለባለሥልጣኑ ካላሳወቀ ብር 10,000፣
- መሣሪያው ያለበትን ትክክለኛ አድራሻ ለባለሥልጣኑ ያላሳወቀ እንደሆነ ብር 50,000፣
- የአድራሻ ወይም የስም ለውጥ ሲያደርግ ወይም የንግድ ሥራውን ሲያቋርጥ ከሦስት ቀናት አስቀድሞ ለአገልግሎት ማዕከሉና ለባለሥለጣኑ ያላሳወቀ እንደሆነ ብር 25,000፣
- መሣሪያው ባለበት የንግድ ሥራ ቦታ በህጉ የተዘረዘሩ አስፈላጊ መረጃዎችና ስታወቂያዎች ካልተቀመጡ ብር 10,000፣
- የሽያጭ ነቁጣ ሶፍት ዌር ዕውቅና ባልተሰጠው ሰው አስቀይሮ ወይም እንዲሻሻል አድርጐ ከተገኘ ብር 30,000 ይቀጣል፡፡
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም የሶፍትዌር አቅራቢነት ፈቃድ የተሰጠው ሰው፣ የንግድ ሥራውን የአድራሻ ለውጥ ለባለሥልጣኑ ካላሳወቀ ብር 100,000፣
- ዕውቅና ያልተሰጠውን መሣሪያ ለገበያ ከዋለ ብር 500,000፣

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.2. ህጋዊ ውጤቶች

2.2.4.ከሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ

- ለእያንዳንዱ መሣሪያ የመለያ ቁጥር ከባለሥልጣኑ ካልወሰደ ወይም የወሰደውን መለያ ቁጥር ለእይታ በሚያመች ቦታ በመሣሪያው ላይ ካልጠፈ ብር 50,000፣
- በመሣሪያው ላይ የሚደረግን ማናቸውንም ለውጥ ለባለሥልጣኑ በቅድሚያ ካላሳወቀ ወይም በአጠቃቀም መመሪያው ውስጥ ስለመረጃው ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ካስገባ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ከቀነሰ ብር 100,000፣
- የማይሰራ፣ የተበላሸ (የተጐዳ) መሣሪያ ለአገልግሎት ማዕከላት በሦስት ቀናት ውስጥ አቅርቦ ማስቀየር (መተካት) አለመቻሉን ለባለሥልጣኑ አስቀድሞ ካላሳወቀ ብር 50,000፣
- ስለተዋዋለባቸው አገልግሎት ማዕከላት መረጃ ካልያዘ ወይም ለባለሥልጣኑ ካላሳወቀ ብር 50,000 ይቀጣል።

• የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አገልግሎት ማዕከል።

- የፊሲካል ማስታወሻ በተተካ በሁለት ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ካላሳወቀ ብር 25,000፣
- ውል የገባባቸውን መሣሪያዎች በዓመት አንድ ጊዜ የቴክኒክ ምርመራ ካላደረገ ብር 25,000፣
- ዕውቅና ያልተሰጠውንና በባለሥልጣኑ ያልተመዘገበ ሠራተኛ ለሥራ አሰማርቶ ከተገኘ ብር 50,000 ይቀጣል።

2.2. ህጋዊ ውጤቶች

2.2.5. ልዩ ልዩ ቅጣቶች

- በንግድ ሥራው ላይ ማንኛውንም ለውጥ ያላሳወቀ ብር 20,000፣
- የመመስረቻ ጽሁፍ (የመተዳደሪያ ደንብ) ወይም የነዚህን ማሻሻያዎች ያላቀረበ ላላቀረበበት ለእያንዳንዱ ቀን ብር 10,000፣
- የኦዲት ሪፖርት እንዲያቀርብ ተጠይቆ ለባለሥልጣኑ ያላቀረበ ማንኛውም ኦዲተር በፈቃዱ ላይ ከሚወሰደው እርምጃ በተጨማሪ ሰነዱ ሳይቀርብ ለቀረበት በእያንዳንዱ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነ ጊዜ ብር 10,000፣
- በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ካልሆነ ሰው ጋር የአገልግሎት ውል የተዋዋለ ሰው መረጃውን ለባለሥልጣኑ ያልሰጠ እንደሆነ ይህንኑ ባላሳወቀበት በእያንዳንዱ ቀን ብር 1,000፣
- ግንኙነት ካለው ሰው ጋር የተደረጉ ግብይቶችን በሚመለከት መረጃ ያላቀረበ ግብር ከፋይ ብር 100,000፣
- መረጃ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ባለሥልጣኑ የሚጠይቀውን መረጃ ያልሰጠ እንደሆነ መረጃውን ተጠይቆ ያልሰጠው ሰው ወይም እንደሁኔታው መረጃ የተጠየቀው መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ብር 5,000 ይቀጣል፡፡

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.2. ህጋዊ ውጤቶች

2.2.6. ወንጀል ተጠያቂነት

- ማንኛውም ሰው ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የወሰደ፣ ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት የሰጠ፣ የሌላውን ሰው የተጠቀመ እንደሆነ ብር 20,000 የገንዘብ ቅጣት እና ከ1-3 ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት፤
- ያለደረሰኝ ግብይት ማከናወን ከብር 25,000 እስከ 50,000 እና ከ3-5 ዓመት ጽኑ እስራት፤
- ለተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይመዘገብ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሰጠ ብር 200,000 መቀጮና ከ7-10 ዓመት ጽኑ እስራት፤
- በተመሳሳይ የደረሰኝ ቅጂዎች ላይ የተለያዩ ዋጋዎችን በመመዝገብ የሽያጭ ዋጋን ማሳነስ ብር 100,000 እና ከ5-7 ዓመት ጽኑ እስራት፤
- ለአንድ ግብይት በተሰጠ ተመሳሳይ ደረሰኝ ላይ የተለያዩ ዋጋዎችን በመመዝገብ የሽያጭ ዋጋን ያሳነሰ ወይም የሽያጭ ዋጋን በማሳነስ ደረሰኝ የሰጠ ማንኛውም ሰው ብር 100,000 የገንዘብ መቀጫ እና ከ5-7 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት፤
- የሀሰት ወይም አሳሳች መግለጫዎችንና የተጭበረበሩ ሰነዶች ለባለሥልጣኑ ያቀረበ ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 ሚደርስ መቀጫና ከ3-5 ዓመት ጽኑ እስራት፤
- ግብይት ሳይፈፀም ደረሰኝ የሰጠ ወይም የተቀበለ ከብር 100,000 እስከ 200,000 እና ከ7-10 ዓመት ጽኑ እስራት፤

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.2. ህጋዊ ውጤቶች
2.2.6. ወንጀል ተጠያቂነት

- በባለሥልጣኑ ሳይፈቀድ ታክስ ደረሰኝ ያተመ ሰው ከብር 300,000 እስከ ብር 500,000 የሚደርስ የገንዘብ መቀጮና ከ2-5 ዓመት ጽኑ እስራት ያስቀጣል፤
- የህገ ወጥ ህትመት የተፈፀመው ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ የህትመት መሣሪያውና ድርጅቱ ይወረሳሉ፡፡
- ማንኛውም ታክስ ከፋይ ደረሰኝ ባለመስጠት ወንጀል ተጠያቂ የሚሆነው የወንጀሉ ድርጊት የተፈፀመው በአንድ የግብር ዘመን ውስጥ ለሁለት ጊዜያት ያህል አስተዳደራዊ ቅጣት ከተቀጣ በኋላ በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡
- የማይገባውን የታክስ ተመላሽ ወይም ማካካሻ የጠየቀ ሰው ብር 50,000 እና ከ5-7 ዓመት ጽኑ እሰረታት ይቀጣል፡፡ ታክስ ከፋዩ የተደረገለትን ታክስ መልሶ ከመክፈል ግዴታ ነፃ ሊሆን አይችልም፤
- የተጭበረበሩ ወይም ህገ ወጥ ደረሰኞችን ያዘጋጀ ያተመ የሸጠ ያሰራጨ ወይም የተጠቀመ ሰው ብር 100,000 እና ከ7-10 ዓመት ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
- የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ማስታወሻ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም በህግ ከተፈቀደው ውጪ የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ማስታወሻ (note) የሰጠ በብር 10,000 እና በአንድ ዓመት ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.2. ህጋዊ ውጤቶች

2.2.6. ወንጀል ተጠያቂነት

- የቴምብር ቀረጥ ያልተከፈለበትን ሰነድ ሥራ ላይ ማዋል ወይም በሰነዱ ላይ መፈረም የቴምብር ቀረጥ ላለመክፈል በማሰብ የሰነዱን ትክክለኛ ባህሪ አለመግለጽ ወይም መደበቅ ከ25,000 እስከ 50,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮና ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
- ቴምብሮችን እንዲሸጥ የተፈቀደለት ሰው የቴምብር ቀረጥ አዋጁን የተላለፈ እንደሆነ ወይም የቴምብር ቀረጦችን ወይም ቴምብር የታተመባቸውን ሰነዶች ሳይፈቀድለት የሸጠ ወይም ለሽያጭ ያቀረበ ሰው ከብር 5,000 እስከ 25,000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና ከሦስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
- የታክስ ከፋይ ንብረት የያዘ ሰው በታክስ ህጐ የተደነገገውን ግዴታ ካልተወጣ በብር 5,000 የገንዘብ ቅጣት እና በአንድ ዓመት ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡
- የንብረት መያዝ ትዕዛዝ የደረሰው ሰው ንብረቱን የሸጠ፣ የለወጠ ወይም በሌላ ማንኛውም መንገድ ያስተላለፈ እንደሆነ ንብረቱን የደበቀ፣ የሰበረ፣ ያበላሸ ወይም የጐዳ፣ ንብረቱን የሚመለከት ማናቸውንም ሰነድ ያወደመ፣ የደበቀ፣ ያስወገደ፣ የጐዳ፣ የለወጠ፣ የሰረዘ፣ የደለዘ ወይም ያጠፋ እንደሆነ ከ2 እስከ 3 ዓመት በሚደረስ ቀላለ እስራት ይቀጣል፡፡

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.2. ህጋዊ ውጤቶች

2.2.6. ወንጀል ተጠያቂነት

- የግብር ከፋዩን ገንዘብ የያዘ ሰው ገንዘቡን ለባለሥልጣኑ ገቢ እንዲያደርግ ታዝዞ ገቢ ያላደረገ እንደሆነ ከ2 እስከ 3 ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡
- ከሀገር የመውጣት እገዳን የጣሰ ሰው ከ2 እስከ 3 ዓመት በሚደርስ ቀላል እሰራት ይቀጣል፡፡
- የገንዘብ ተቋም በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 42 የተመለከተውን ግዴታ ካልተወጣ ባለሥልጣኑ በዚያ ምክንያት ሳይሰበሰብ በቀረው የገንዘብ መጠን ይቀጣል፡፡
- የገንዘብ ተቋሙ ግዴታውን ያልፈጸመው ሥራ አስኪያጁ እያወቀ ወይም በሥራ አስኪያጁ ቸልተኝነት ከሆነ ሥራ አስኪያጁ ከ2 እስከ 3 ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡
- በባለሥልጣኑ የተደረገን እሽግ የከፈተ ወይም ያስወገደ ከ2 እስከ 3 ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡
- ታክስ ላለመክፈል ወይም ገቢን ለመሰወር በማሰብ ገቢን የደበቀ ወይም የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ወይም ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ ከብር 100,000 እስከ 200,000 የገንዘብ መቀጮና ከ3 እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.2. ህጋዊ ውጤቶች

2.2.6. ወንጀል ተጠያቂነት

- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ቀንሶ የያዘውን ታክስ ለባለሥልጣኑ ገቢ ያላደረገ ግብር ከፋይ ከ3 እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
- የታክስ ህጎችን አስተዳደር ያደናቀፈ ማንኛውም ሰው ከ1 እስከ 3 ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡
- ሥልጣን ሳይኖረው ታክስ የሰበሰበ ወይም ለመሰብሰብ የሞከረ ሰው ከ5 እስከ 7 ዓመት በሚደረስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
- አንድ የታክስ ወንጀል ሲፈጸም የረዳ፣ ያበረታታ ወይም የተባበረ፣ ያገዘ፣ ያነሳሳ እንደሆነ በዋና አድራጊው ላይ የሚወሰነውን ቅጣት ይቀጣል፡፡
- የታክስ ይግባኝ ኮሚሽኑን ሥራ ያሰናከለ ሰው ከስድስት ወር እስከ 2 ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡
- ማንኛውም ሰው የታክስ ወኪልነት ፈቃድ ሳይሰጠው የታክስ ወኪልነት አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ ከ1 እስከ 3 ዓመት በሚደረስ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.2. ህጋዊ ውጤቶች
2.2.6. ወንጀል ተጠያቂነት

- በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ሰው በባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተሰጠው ወይም ያልተመዘገበ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከተጠቀመ ከ3 ዓመት በማያንስ እና ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤
- መሣሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ወይም በሌላ በቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጪ ወይም ያለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ ከሁለት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤
- በሽጭያ መመዝገቢያ መሣሪያው የፊሲካል ማስታወሻ ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም እንዲቀየር ማድረግ ወይም እነዚህን ድረጊቶች ለመፈፀም መሞከር ከ3 ኣመት በማያንስ እና ከ5 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ያስቀጣል፤
- እውቅና የተሰጠው የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ወይም ሶፍት ዌር አቅራቢ ከባለሥልጣኑ ዕውቅና ያልተሰጠው መሣሪያ ወይም ሶፍት ዌር ለገበያ ካዋለ ከ3 ዓመት በማያንስ እና ከ5 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.2. ህጋዊ ውጤቶች
2.2.6. ወንጀል ተጠያቂነት

- በሥራ ላይ ባሉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ለውጥ ለባለሥልጣኑ በቅድሚያ አለማሳወቅ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ማስገባት ወይም መረጃ መቀነስ ከ3 አመት በማያንስ እና ከ5 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት
- የሽጭያ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም የፊሲካል ማስታወሻ አቅራቢነት ፈቃድ ሳይኖር የሽጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ወይም የፊሲካል ማስታወሻ ለገበያ ማዋል ከ5 ዓመት እስከ 7 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ያስቀጣል፤
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች የአገልግሎት ማእከል አቅራቢ ዕውቅና ያልተሰጠው እና በባለሥልጣኑ ያልተመዘገበ ሰራተኛ በሥራ ላይ አሰማርቶ ከተገኘ 50 ሺ ብር የገንዘብ ቅጣት ወይም ከ1 ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ያስቀጣል፤
- የማዕከሉ ሰራተኛ የሽጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ያለአገልግሎት ማእከሉ እና ያለባለሥልጣኑ ዕውቅና ከፈታታ ወይም ከገጣጠም ወይም እሽጉን ካነሳ ወይም አካሉን ከቀየረ ወይም እነዚህን የመሳሰሉ አድራጎቶች ከፈፀመ ከብር 10 ሺ በማይበልጥ የገንዘብ ቅጣት እና ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሶስት ዓመት በማበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፤

2. የግብር ከፋዮች ግዴታና ህጋዊ ውጤቱ

2.2. ህጋዊ ውጤቶች
2.2.6. ወንጀል ተጠያቂነት

- የታክስ ሰራተኛ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የፈታ ወይም የገጣጠመ ወይም የአገልግሎት ማዕከል ሰራተኛ በሌለበት ሥራ ላይ እንዲውል የፈቀደ ወይም የመሣሪያውን መለያ የቀያየረ እንደሆነ ወይም ማናቸውንም ህገ ወጥ ድርጊት እያወቀ ወይም በቸልተኝነት በ24 ሰዓት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ያላደረገ እንደሆነ ከብር 5 ሺ በማይበልጥ የገንዘብ ቅጣት እና ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።
- የታክስ ህግን በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመው ድርጅት ወይም የሕግ ሰውነት የተሰጠው በግለሰብ ባለቤትነት ሥራ ያለ የንግድ ሥራ በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ በተፈጸመበት ወቅት የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ፤ የፋይናንስ ኃላፊ ወይም በተመሳሳይ የኃላፊነት ቦታ ላይ ያለ ሰው ወንጀሉን እንዲፈጸም ይቆጠራል።
- ስራ አስኪያጁ፤ የፋይናንስ ኃላፊው ወይም በተመሳስይ የኃላፊነት ቦታ ላይ ያለው ሰው የሚከተሉትን ያስረዳ እንደሆነ በወንጀሉ ተጠያቂ አይሆንም፦
  - ሀ) ወንጀሉ የተፈጸመው ከርሱ እውቅና ውጪ መሆኑን፤
  - ለ) ወንጀሉ እንዳይፈጸም ያልፈቀደ፣ ያላዘዘ ወይንም ያልተባበረ መሆኑን፤ ወይም
  - ሐ) የዚህ አይነቱ ወንጀል እንዳይፈጸም መከላከል የሚያስችል ውስጥ ቁጥጥር ስርአት የዘረጋ መሆኑን፤

እናመሰግናለን !